# አዲስ ዘመን

አንድ

ማክሰኞ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 211 ሚያዝያ 1 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





# “በቴክኖሎጂ ፈጠራ ሃሳቦች ላይ መዋዕለ ንዋያቸውን ለሚያፈሱ እንደሀገር ምቹ ሁኔታዎች አሉ”

- እዮብ ተካልኝ
የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- በቴክኖሎጂ ፈጠራ ሃሳቦች ላይ መዋዕለ ንዋያቸውን ለሚያፈሱ ኢንቨስተሮች እንደሀገር ምቹ ሁኔታዎች መኖራቸውን የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ እዮብ ተካልኝ ተናገሩ፡፡

“የኢትዮጵያ ስታርት አፕ” ዓውደ ርዕይ በሳይንስ ሙዚየም ሲካሄድ ሚኒስትር ዴኤታው እዮብ ተካልኝ ለጋዜጠኞች በሰጡት ሃሳብ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ አፍሪካን ብሎም ለዓለምን ዘርፈ ብዙ ችግሮች መፍትሔ ማምጣት የሚያስችሉ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ሃሳብ ያላቸው ወጣቶች መታየት ጀምረዋል፡፡ በመሆኑም ኢንቨስተሮች መዋዕለ ንዋያቸውን በፈጠራ ሃሳቦቹ ላይ በማፍሰስ በጋራ መሥራትና ሀገርን የሚለውጥ ተግባር ላይ መሳተፍ ይገባቸዋል ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በስታርት አፕ ዓውደ ርዕዩ እንደታየውም በኢንጂነሪንግ ዘርፍ፣ በፋይናንስ ክፍያ ሥርዓት ማዘመን፣ በጤናው መስክ፣ በግብርናውና በግንባታው ዘርፍ በወጪ ቅነሳ ላይ እንዲሁም በተለያዩ መስኮች ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረጉ የፈጠራ ሥራዎች መውጣት ጀምረዋል ሲሉ አቶ እዮብ ተናግረዋል፡፡

ፈጠራዎቹን በስፋት ወደ ሥራ ለማስገባት ደግሞ ኢንቨስት የሚያደርግ አካል ስለሚያስፈልግ ባለሃብቶች ውጤታማነታቸውን አይተው ሊሳተፉ እንደሚገባ አመልክተዋል፡፡


ተስፋ ሰጪ ውጤት ያለው ሃሳብና ፋይናንስ ሲገጣጠሙ በእራሱ ውጤታማ መሆን ይቻላል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ መንግሥት በባንኮች በተለይም በልማት ባንክ በኩል በቴክኖሎጂ ላይ ለተመሠረቱ የፈጠራ ሃሳቦች ፈንድ የሚያቀርብበትን አሠራር ማመቻቸቱን አስረድተዋል፡፡

ባለሃብቶች በበኩላቸው በኢትዮጵያ ትልቅ የልማት ሥራ ማከናወን የሚችሉባቸውና በገቢም ረገድ ትልቅ ለውጥ ማምጣት የሚችልባቸው


“በቴክኖሎጂ ፈጠራ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል




ፎቶ-ሀዲሽ አብርሀ



# የአፈር ጤና ለሀገር ሕልውና

አዲሱ ገረመው

የኢትዮጵያ የአፈር ሀብት መረጃ ፕሮጀክት ጥናት እንደሚያሳየው እየታረሰ ካለው የመሬት ሽፋን 43 በመቶው በአሲዳማነት የተጠቃ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥም 28 በመቶ በጠንካራ አሲዳማነት፣ ሲሆን ይህም አጠቃላይ ከሚታረሰው መሬት ሦስት ነጥብ አንድ


የአፈር ጤና ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል




ሲቀ ትጉሐን ቀሲስ ታጋይ ታደሰ

# ሃይማኖትን ሽፋን አድርገው የተከሰቱ ግጭቶችን በመፍታት ረገድ አመርቂ ውጤት ተመዝግቧል


ገጽ 6


# የጠቅላይ ሚኒስትሩ የሩዋንዳ ቆይታ የሁለቱን ሀገራት ትስስር ይበልጥ የሚያጠናክር ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) በሩዋንዳ ኪጋሊ ያደረጉት ኦፊሴላዊ ቆይታ የሁለቱን ሀገራት ትስስር ይበልጥ የሚያጠናክር መሆኑን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ፕሬስ ሴክሬታሪያት ኃላፊ ቢልለኔ ሥዩም ገለጹ፡፡

ኃላፊዋ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) በሩዋንዳ ኪጋሊ ያደረጉትን ኦፊሴላዊ ጉብኝት በተመለከተ በሰጡት ማብራሪያ እንዳሉት፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከልዑካን ቡድናቸው ጋር ያደረጉት ቆይታ የሁለቱን ሀገራት ትስስር ይበልጥ የሚያጠናክሩ ተግባራት የተከናወኑበት ነው፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የኪጋሊ ኦፊሴላዊ ጉብኝት ሁለት ዓላማዎች እንደነበሩት ጠቅሰው፤ የመጀመሪያው ዓላማ ከሩዋንዳ ፕሬዚዳንት ፖል ካጋሜ ጋር ስኬታማ የሁለትሽ ውይይት የተካሄደበት ነው፡፡ ሁለተኛው ዓላማ ደግሞ የኪዊቡካ 30ኛ ዓመት መታሰቢያ ላይ በመገኘት ኢትዮጵያ ከሩዋንዳውያን ጋር


የጠቅላይ ሚኒስትሩ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል







# ‹‹ኢድ አልፈጥርን በአንድነት በመደጋገፍ እና በመተሳሰብ የምናሳልፈው በዓል ሊሆን ይገባል››

- ሐጂ ሙስጠፋ ናስር

የኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ሥራ አስፈጻሚ እና የሠላምና የእርቅ ዘርፍ ኃላፊ

**ዘሳለም ግዛው**



አዲስ አበባ፡- ኢድ አልፈጥር በዓልን የምናከብረው በአንድነት በመተሳሰብ እና በመደጋገፍ ነው ሲሉ የኢትዮጵያ የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ሥራ አስፈጻሚ እና የሠላምና የእርቅ ዘርፍ ኃላፊ ሐጂ ሙስጠፋ ናስር ገለጹ።

ሙስሊሙ ኅብረተሰብ እንኳን ለአንድ ሺህ 445 ኛውን የዒድ አል ፈጥር በዓል በሰላም አደረሳችሁ። በዓሉ የሠላም፣ የደስታ፣ የመከባበር፣ የመበልጸግ እና የመተባበር እንዲሆን እመኛለሁ፣ በዓሉ መተሳሰብን የሚያጠናክር አብሮነትን የሚያጸና ነው ሲሉ አመልክተዋል።

የእስልምና ተከታዮች የሆንን ሁሉ በዓሉን ስናከብር የታመሙ በመጠየቅ፣ አስታዋሽ የሌላቸውን በመደገፍ እና በመርዳት በዓሉን በጋራ እየተደሰትን ማሳለፍ ይገባናል ሲሉም ሐጂ ሙስጠፋ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

ሙስሊሞች በዓሉን ስናከብር በእለቱ ለድሆች የምንሰጠው አለን። ከዛም ባለፈ ደካሞችን በመዘየር ለተቸገሩ በመርዳት፣ የታረዙትን በማልበስ፣ የተራቡትን በማብላት መሆን ይገባል።

በሸሪያችን መሠረትም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ያዘዙንን በመፈጸም ማክበር ይጠበቅብናል ያሉት ሐጂ ሙስጠፋ፤ ስንደሰት ለሰው ሁሉ መልካም ልናስብ እና ልናደርግ ይገባናል። አካባቢያችን የሚኖሩ የሰው ልጆችን ያለልዩነት በአንድነት ማሳለፍ ይገባናል ነው ያሉት።

በዓል ነው ብለን የምናሳልፈው ሳይሆን 30 ቀናት የፆምነው ፆማችን ተቀባይነት አግኝቷል ወይ ብለን በዱአ ደካሞችን በመደገፍ የምናሳልፈው ቀን እንደመሆኑ ሙስሊሙ ይህንን በማሰብ ማሳለፍ አለበት። ሕዝበ ሙስሊሙ በረመዳን ወር በመደጋገፍ በመተዛዘን በፆም በዱዓና በትጋት አሳልፏል ነው ያሉት።

አላህ ለሀገራችን ሠላም እንዲሰጥ እንፀልያለን። ለመንግሥታችንም ለሕዝቦቹ የሚራራ እና የሚያዝን እንዲሆን፣ ሕዝብም ለመንግሥት ታዛዥ እንዲሆን አላህን እንለምናለን ብለዋል።

ሁሉም የሠራው ተሳክቶለት ርካታ የሚያገኝበት ዘመን እንዲያደርግልን እንማጸናለን ብለዋል። የኢትዮጵያ እድገት ቀጥሎ ሠላም እንዲሰፍን ተማጽነዋል።

ግጭቶችን አላህ እንዲያበርዳቸው ዱአ ማድረግ አለብን በማለትም መልእክት አስተላልፈዋል። የረመዳን ወቅትን በመቻቻል፣ በመከባበር የፆሙን ጊዜ አሳልፈናል፣ ዘካ የሚሰጡ ባለሃብቶች ለድሆች ዘካ እየሰጡ፣ ድሆችን የሚያበሉም እየመገቡ እስካሁን በስኬት አሳልፈናል። የነበረው መልካምነት ይቀጥላል።

የነበሩ ጥቃቅን ችግሮች እና ልዩነቶች በሠላም እየተፈቱ ፆሙን መጨረስ ችለናል። ዒዱ የሠላም የመተጋገዝ እና የአንድነት እንዲሆን እመኛለሁ ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# የፀረ ሙስና ትግሉን ከግብ ለማድረስ የፍትሕ ተቋማት በቅንጅት ሊሠሩ ይገባል

**ሄለን ወንድምነው**



አዲስ አበባ፡- የፀረ ሙስና ትግሉን ከግብ ለማድረስ የፍትሕ ተቋማት በቅንጅት ሊሠሩ እንደሚገባ የአዲስ አበባ ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ከከተማ አስተዳድደሩ ፍትሕ ቢሮና ፖሊስ ኮሚሽን ጋር ትናንት የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርሟል።

የአዲስ አበባ ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀማል ረዲ በወቅቱ እንደገለጹት፤ በመዲናዋ የተጀመረውን የፀረ ሙስና ትግል ከግብ ለማድረስ የፍትሕ ተቋማት በቅንጅት መሥራት ወሳኝ ነው።

ሙስናና ብልሹ አሠራርን መታገል በአንድ ተቋም ብቻ የሚሠራ ባለመሆኑ የሙስና ትግሉን በተጠናከረ መልኩ ለመሥራት የፍትሕ ተቋማትን ቅንጅት እና የእያንዳንዱን ማኅበረሰብ እገዛ እንደሚጠይቅ አስታውቀዋል።

ሙስናና ብልሹ አሠራር ሀገርንና ትውልድን የሚጎዳ ትልቅ ችግር በመሆኑ በዚህ ተግባር ላይ የተሠማሩ ዜጎችን በሕግ ተጠያቂ ማድረግ ይገባል ብለዋል።

ሙስናን ለመዋጋት በሚደረግ የጋራ ጥረት የትብብር ማዕቀፍን ለመመሥረት ኮሚሽኑ ከከተማ አስተዳደሩ ፍትሕ ቢሮና ፖሊስ ኮሚሽን ጋር በጋራ መሥራት የሚያስችለውን የመግባቢያ ስምምነት መፈራረሙን ገልጸው፤ ስምምነቱ በመንግሥት ተቋማት ሕጋዊና አስተዳደራዊ ተጠያቂነት ለማስፈን፣ ለፀረ ሙስና ትግሉ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር እንዲሁም ሀብትን፣ እውቀትንና ሥልጣንን ለማቀናጀት ያግዛል ነው ያሉት።

በፀረ ሙስና ትግሉ ውስጥ ከጥቆማ እስከ ተጠያቂነት ድረስ ያለውን መረጃ ለመለዋወጥ፣ የጋራ ጥናት ለመሥራት እና ኅብረተሰቡ ሙስናን መዋጋት የሚያስችለውን የጋራ ግንዛቤን ለመፍጠር እንደሚሠራም ጨምረው ገልጸዋል።

የመግባቢያ ስምምነቱ የፀረ ሙስና ትግሉን ውጤታማ ለማድረግ እገዛ ያደረጋል ያሉት ኮሚሽነር ጀማል፤ ለሁለት ዓመት እንደሚተገበር ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጌቱ አርጋው በበኩላቸው፤ ስምምነቱ በከተማ ደረጃ ያለውን ሙስና በጋራ ለመከላከልና የፀረ ሙስናን ትግሉን ለኅብረተሰቡ ለማስገንዘብ ያግዛል።

ሙስናን በመከላከል ረገድ እንደ ተቋም በተናጠል የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት አጠናክረው እንደሚያስቀጥሉ ገልጸው፤ ከፍትሕ አካላትም ጋር በመቀናጀት ሙስናን የመከላከልና የሙስና ወንጀል የሚፈጽሙ አካላትን በሕግ ተጠያቂ የማድረግ ሥራ እንደሚሠሩ አመልክተዋል።

በመዲናዋ ሙስናን በመከላከል በተሠሩት ሥራዎች ሥልጣንን በአግባቡ ካለመጠቀም፣ ከግብር፣ ከመሬት፣ ከሐሰተኛ ሰነድ፣ አገልግሎትን በገንዘብ የሚሸጡና እና ሌሎች የማጭበርበር ወንጀሎችን የፈጸሙ አካላትን ተጠያቂ የማድረግ ሥራ በመሠራቱ ተጨባጭ ውጤት ማምጣት መቻሉን አስረድተዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትሕ ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ተስፋዬ ደጀኔ በበኩላቸው፤ ለፍትሕ ቢሮ የሚቀርቡትን ጥቆማዎች በመመርመር ለሚመለከተው አካል የማቅረብ፣ ውጤቱን የመከታተል፣ በከተማ አስተዳደሩ የተመዘበሩ የመንግሥትና የሕዝብ ሀብትን የማስመለስ፣ ኅብረተሰቡ ሙስናን እንዲጸየፍ ግንዛቤ የመፍጠር እና ሌሎች ሥራዎችን እንደሚሠሩ አስታውቀዋል።

በስምምነቱ የአዲስ አበባ ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀማል ረዲ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጌቱ አርጋውና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትሕ ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ተስፋዬ ደጀኔ ተፈራርመዋል።

# ቀይ መስቀል የተጓተተውን የሕንጻ ግንባታ ከንግድ ባንክ ጋር አልምቶ ለመጠቀም ወሰነ

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ለ28 ዓመታት የተጓተተውን የፍልውኃ ሁለገብ የሕንፃ ግንባታ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር አልምቶ ለመጠቀም መወሰኑን አስታወቀ።

የማኅበሩ ፕሬዚዳንት አቶ አበራ ቶላ እንደገለፁት፤ ማኅበሩ ሰሞኑን ልዩ ብሔራዊ ጠቅላላ ጉባኤ አካሂዷል።

ጠቅላላ ጉባኤው የፍልውሃ ፕሮጀክት የግንባታ ሂደት ከተጀመረ 28 ዓመት ቢሆንም እስካሁን በተሠራው ሥራ ከምድር ከፍ ማለት ባለመቻሉ ቦርዱ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር በጋራ በማልማት የጋራ ሀብት እንዲሆን የጀመረውን ሂደት ከክልል፣ ከዞንና ከወረዳ ቅርንጫፍ አመራሮች ጋር በመወያየት ከውሳኔ ላይ ደርሷል ብለዋል።

የሕንጻ ግንባታው ለ28 ዓመታት ሲጓተት መቆየቱን ያነሱት አቶ አበራ፤ ግንባታውን የተቀበሉ ሥራ ተቋራጮች ባሳዩት አነስተኛ አፈጻጸም፣ በተለያዩ አደጋዎች፣ በኮቪድ ወረርሽኝና በተለያዩ ጊዜያት በተከሰቱ ግጭቶች ምክንያት ማኅበሩ ግንባታውን ከማከናወን ይልቅ ለዜጎች የሰብዓዊ ርዳታዎችን በማቅረብ ላይ በመጠመዱ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

የማኅበሩ ባለፉት አራት ዓመታት የሕንፃ ግንባታውን በራሱ ወጪ ለማከናወን የተለያዩ አማራጮች ቢፈልግም ሊሳካለት እንዳልቻለ አስታውሰው፤ ከባንኮች ብድር በመውሰድ ግንባታው ለማከናወን የአዋጭነት ጥናት ቢሠራም የማይችል መሆኑ እንደተነገራቸው ጠቁመዋል።

ግንባታውን ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር በጋራ ለማልማት በድርድር ላይ እንደሚገኝ የገለጹት ፕሬዚዳንቱ፤ ግንባታው ሲጠናቀቅም ማኅበሩ ለግንባታው ሂደት ባወጣው ልክ ድርሻ የሚኖረው ሲሆን፤ ማኅበሩ ዜጎችን ለመረዳት የቆመለትን ዓላማ ለማሳካት ጉልህ አስተዋፅዖ ይኖረዋል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ምክትል ፕሬዚዳንት ኤፍሬም መኩሪያ በበኩላቸው፤ የፍልውኃ ፕሮጀክት ከተጀመረ ሦስት አስርተ ዓመታት ሊሞላው መቃረቡን አንስተው፤ ከጥቂት ወራት በፊት የማኅበሩ ብሔራዊ ቦርድ ለባንኩ በጋራ እንሥራ የሚል ሀሳብ ካቀረበ ወዲህ ባንኩ የበለጠ ትኩረት በመስጠት ንግግሮችን እያደረገ እንደሚገኝ አመልክተዋል።

እንደ አቶ ኤፍሬም ገለጻ፤ ከማኅበሩ ቦርድ አመራሮች ጋር በተደረገ ውይይት ሁለቱም ተቋማት የሀብቱ ባለቤት ሆነው ግንባታውን ማከናወን እንደሚችሉ ውሳኔ ላይ ደርሰዋል።

ግንባታውን ለማከናወን ከቁፋሮ ጀምሮ ማህበሩ ያወጣውን ወጪና የይዞታው ባለቤትነት ከግምት በማስገባት ድርሻው እንደሚወሰንና ለግንባታው የሚያስፈልገውን ወጪ ባንኩ እንዲያቀርብ ከስምምነት ለመድረስ ታቅዷል ሲሉ ተናግረዋል።

ከሚደረገው ስምምነት በኋላ ባንኩ ሙሉ የግንባታውን ሂደቱ ላይ ኃላፊነት በመውሰድ የግንባታውን ዲዛይን በማሻሻልና አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎችን በሟሟላት ግንባታው በፍጥነት እንዲከናወን እንደሚሠራ ምክትል ፕሬዚዳንቱ አስታውቀዋል።

# በክልሉ ዘንድሮ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር አንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ችግኞች ይተከላሉ

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡ በአማራ ክልል በዘንድሮ ክረምት በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር አንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ችግኞች እንደሚተከሉ የክልሉ ግብርና ቢሮ ገለጸ።

በአማራ ክልል ግብርና ቢሮ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃ እና አጠቃቀም ዳይሬክተር አቶ ዘላለም ምሕረት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ በዘንድሮ ክረምት በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር በአጠቃላይ አንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ችግኞች ለመትከል ታቅዶ ዝግጅቶች እየተደረጉ ነው።

እስከ አሁን ድረስ ከ280 ሚሊዮን በላይ ለቆጠራ የደረሱ ችግኞች የተዘጋጁ ሲሆን ከተዘጋጁት ችግኞች 42 ነጥብ ሁለት በመቶ አገር በቀል ዝርያዎች መሆናቸውን ጠቅሰዋል። የችግኝ ዝግጅቱ ሚያዚያ ወር መጨረሻ ድረስ ይጠናቀቃል ተብሎ እንደሚጠበቅም ገልፀዋል።

ችግኝ ከመፈላቱ በፊት አስቀድሞ የተከላ ቦታ የመለየት ሥራ መሠራቱን የተናገሩት ዳይሬክተሩ፤ በአጠቃላይ ከታቀደው 221ሺ ሄክታር በላይ የተከላ ቦታ እስከ አሁን ድረስ ከ117ሺ ሄክታር በላይ ቦታ መለየቱን ተናግረዋል።

በዘንድሮ ክረምት በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ለመትከል ከታቀዱት ችግኞች 18 ነጥብ አምስት ሚሊዮን የሚሆኑት የአቮካዶ፣ ማንጎና ሌሎች ፍራፍሬዎች መሆናቸውን ጠቁመው፤ እስከ አሁን ወደ 11 ሚሊዮን የሚጠጉ የፍራፍሬ ችግኞች መዘጋጀታቸውን ጠቅሰዋል።

በክልሉ በአብዛኛው ተከላ የሚጀመረው በሰኔ ወር መጨረሻ ወይም በሐምሌ ወር መጀመሪያ መሆኑን አስታውሰው፤ በዘንድሮ ዓመትም እንደዝናቡ ሁኔታ የሚወሰን ሆኖ በእቅድ ደረጃ በተመሳሳይ ጊዜ መያዙን ተናግረዋል።

ባለፈው ዓመት የተተከሉ ችግኞችን የመንከባከብ ሥራዎች መሠራታቸውንና የመጀመሪያው ዙር የፅድቀት ምጣኔ 91 በመቶ መሆኑን ገልጸዋል። በቀጣይ ሁለተኛው ዙር የፅድቀት ምጣኔ ታይቶ ለዕድሳት ተከላ ችግኞች እንደሚዘጋጁ ጠቁመዋል።

ለአረንጓዴ ዐሻራ እየተዘጋጁ ያሉ ችግኞች ውሃ በበቂ መጠን አግኝተው ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲዘጋጁ ባለሙያዎች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት አለባቸው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ አርሶ አደሩም የሚተክልበትን ቦታ አዘጋጅቶ መጠበቅ እንዳለበት ጠቁመዋል።

# “ድርጅቱ በቅንጅት ባለመሥራቱ ከአንድ ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ አጥቷል”

### -የመንግሥት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

# “ችግሩ በሁለቱ ድርጅቶች መገፋፋት የመጣ አይደለም”

### - የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ከባለድርሻ አካላት ጋር በዋናነትም ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጋር በቅንጅት ባለመሥራቱ ከአንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ ማጣቱን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አስታወቀ። ድርጅቱ በበኩሉ ችግሩ በሁለቱ ተቋማት መገፋፋት የመጣ አለመሆኑን ገልጿል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የ2014/15 በጀት ዓመት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የኃይል ማስተላለፊያ መስመሮችና ማከፋፈያ ጣቢያዎች ፕሮጀክት አፈጻጸም የክዋኔ ኦዲት ሪፖርትን በትላትናው እለት ገምግሟል።

በወቅቱ የቋሚ ኮሚቴው ዋና ሰብሳቢ የሺእመቤት ደምሴ እንደገለጹት፤ ድርጅቱ የኃይል ማስተላለፊያ መስመሮችንና ማከፋፈያ ጣቢያ ፕሮጀክት መሠረተ ልማት ዝርጋታና የኃይል ደራሽነትን ለማረጋገጥ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመሥራት የሚያስችል ወጥ የሆነ ሥርዓት እንዳልዘረጋ በሪፖርቱ ተቀምጧል።

ኃይል ሲቋረጥ በድርጅቱ እና በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት መካከል ኃላፊነት ወስዶ ችግሮችን በጋራ ለመቅረፍ በእቅድ ላይ የተመሠረተ ሥራ አልተሠራም ያሉት ሰብሳቢዋ፤ በዚህም ከአገልግሎቱ ጋር በቅንጅት ባለመሥራቱ እና የኤሌክትሪክ ኃይል ለሀገር ውስጥ እና ለጎረቤት ሀገሮች ባለመሸጡ በአማካኝ አንድ ቢሊዮን 271 ሚሊዮን 244 ሺህ 977 ብር ድርጅቱ ማጣቱን በ2013 ዓመታዊ ሪፖርት የተገለጸ መሆኑ በኦዲት ሪፖርቱ ተመላክቷል ሲሉ ተናግረዋል ።



የሺእመቤት ደምሴ



ኢንጂነር አሸብር ባልቻ

ሰብሳቢዋ፤ እነዚህ ተቋማት እንደ ሀገር ትልቅ ኃላፊነት የተሰጣቸውና እንደ አንድ የሚታዩ መሆናቸውን ገልጸው፤ ሆኖም በሁለቱ ተቋማት መገፋፋት ምክንያት ሀገሪቱ ማግኘት ያለባትን ገቢ ማጣቷን ተናግረዋል። ለዚህም ድርጅቶቹ ምንም አይነት የሕግ ማዕቀፍ በሌለው መንገድ መሥራታቸው ምክንያት ነው ብለዋል ።

በቀጣይ በሕግ የታሠረ በስምምነት ሰነድ የተደገፈ ቅንጅታዊ አሠራር በአስቸኳይ በመመሥረት ወደ ሥራ መግባት ይኖርባቸዋል ሲሉ አሳስበዋል ።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ዋና ሥራ አስፈጻሚ ኢንጂነር አሸብር ባልቻ በበኩላቸው፤ ድርጅቱ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጋር በተለያዩ ጊዜያት በመገናኘት የእቅድም ሆነ የኦፕሬሽን ሥራዎችን በቅንጅት ተወያይቶ ይሠራል ።

ነገር ግን ቋሚነት ያለው የተፈረመ ሰነድ በሁለቱ ድርጅቶች መካከል የለም ሲሉ ገልጸው፤  ይህም እንደ ክፍተት የሚወሰድ ይሆናል ብለዋል ።

ከዚህ በፊት የነበረው ችግር አሁን ላይ እየተቀረፈ ይገኛል ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ ችግሩ በሁለቱ ተቋማት መገፋፋት የመጣ አይደለም ሲሉ አፅንዖት ሰጥተው አስረድተዋል።

በተጨማሪም ድርጅቱ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር እንዲሁም ከክልሎች ጋር በጥሩ ግንኙነት  እየተሠራ እንደሚገኝ የተናገሩት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ በቀጣይ በጀት ዓመት ያሉትን ክፍተቶች በማስተካከልና የሕግ ማዕቀፎችን በማዘጋጀት የቅንጅት ሥራውን ለማጠናከር ጥረት ይደረጋል ሲሉ ገልጸዋል ።

# ድጋፉ ማዕከሉ ያለበትን ዋነኛ የትራንስፖርት ችግር የሚቀርፍ ነው

**ማሕሴት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ለመቄዶኒያ የአረጋውያንና አዕምሮ ሕሙማን መርጃ ማዕከል ያደረገው የተሽከርካሪ ድጋፍ ማዕከሉ ያለበትን ዋነኛ የትራንስፖርት ችግር የሚቀርፍ መሆኑ ተገለጸ።

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ለመቄዶኒያ የአረጋውያንና አዕምሮ ሕሙማን መርጃ ማዕከል 3 ነጥብ 8 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ የቢሮ ቁሳቁስ እና 11 ተሽከርካሪዎችን በትናንትናው እለት ድጋፍ አድርጓል።

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ጫልቱ ሳኒ ድጋፉን ባስረከቡበት ወቅት እንደገለጹት፣ ማዕከሉ ሃይማኖት፣ ብሔር፣ ቋንቋ  ሳይለይ ከትንሽ እስከ ትልቅ ያቀፈ ትንሽዋን ኢትዮጵያን የምናይበት ትልቅ ማዕከል ነው።

በተለይም ለሀገር ትልቅ ውለታ የዋሉ አረጋውያንን ማገዝና ውለታ መመለስ የሁሉም ኃላፊነትና የእድሜ ዘመን በረከት የሚያስገኝ ነው ብለዋል።

በዚህም ያለልዩነት አንድነትን በማጠናከር በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ለተለያዩ ችግሮች የተጋለጡና እርዳታን ከሚሹ ወገኖች  ጋር መደጋገፍ ይገባል ብለው፤ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር የሚያደርገውን ድጋፍን



አጠናክሮ እንደሚቀጥል ሚኒስትሯ አስታውቀዋል።

የመቄዶኒያ የአረጋውያንና አዕምሮ ሕሙማን መርጃ ማዕከል መሥራችና ሥራ አስኪያጅ ቢኒያም በለጠ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ሚኒስቴሩ ላደረገው ድጋፍ አመስግነው፤ ድጋፉ በተለይም የማዕከሉን የትራንስፖርት እጥረት የሚፈታ ነው ብለዋል።

እንደ ቢኒያም (ዶ/ር) ገለጻ፤ በማዕከሉ የሚገኙ በቀን እስከ 100 የሚሆኑ ተገልጋዮች ወደ ሕክምና ቦታ መሄድ አለባቸው። እነሱንም በአብዛኛዎቹ አልጋ ቁራኛ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ በትራንስፖርት እጥረት ምክንያት ወደ ሕክምና ቦታ ለመውሰድም ሆነ ማንቀሳቀስ ሲቸገር ቆይቷል።

አሁን ላይ የተደረገው ድጋፍም ያጋጥም የነበረውን የትራንስፖርት እጥረት በመፍታት አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት ያስችላል ብለዋል።

በማዕከሉ በ26 ቅርንጫፎች 7 ሺህ 500 አረጋውያንና የአዕምሮ ሕሙማን እንደሚገኙ ገልጸው፤ በቀጣይም ቅርንጫፎችን ወደ 120 በማሳደግ ከ20 ሺህ በላይ ድጋፍ የሚሹ ዜጎችን ለመጨመር የተያዘውን እቅድም የሚያሳካ መሆኑንም አስታውቀዋል።

በመሆኑም ሁሉም የማኅበረሰብ ክፍል ሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ ያደረገውን መልካም ተግባር አርዓያ በማድረግ የተቸገሩትን ለመርዳት የድርሻውን መወጣት አለበት ብለዋል።

ማዕከሉን በአካል በመምጣት ወይም በ8161 አጭር የጽሑፍ መልዕክት በመላክ እንዲሁም የቁሳቁስና የተለያዩ በዓላትን በጋራ በማዕከሉ በማክበር፣ በሙያዊ ድጋፎች እና ለማዕከሉ በማንኛውም መልኩ የሚደረገው ድጋፍ አጠናክሮ እንዲቀጥልም ቢኒያም (ዶ/ር )ጥሪ አቅርቧል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለበጋ መስኖ ስንዴ ልማት አዝመራ ስብሰባው የበለጠ ውጤታማነት!

በሀገራችን በተለመደው የግብርና ሥራ አሁን ያለንበት ወቅት ለመጪዎቹ የበልግና የመኸር ግብርና ወቅቶች የማሳ ዝግጅት የሚጀመርበት ነው። ለበልጉ ወቅት ከዚህም ያለፈ የሚሠራበትም ነው። በተለይ እንዲህ እንዳሁኑ ዝናብ በሚኖርበት ጊዜ አርሶ አደሩ ለማሳ ዝግጅት ሥራው ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል። ማሳው ከታረሰ የዝናቡን ውሃ በሚገባ በመያዝ መሬቱ እርጥበት እንዲኖረው ማድረግ ያስችላል።

ይህ ወቅት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት አዝመራ ስብሰባ የሚካሄድበት ወሳኝ ወቅት ሆኗል። በአሁኑ ወቅትም የበጋ መስኖ ስንዴ አዝመራ ስብሰባ በስፋት እየተካሄደ ያለበት ሁኔታም ይህንኑ ያመለክታል።

መረጃዎች እንዳመለከቱት፣ በ2016 ዓ.ም የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሦስት ሚሊዮን ሄክታር ማሳ በስንዴ ዘር መሸፈን ተችሏል። ከዚህ ልማት 120 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለማግኘት ታቅዶ ሲሠራም ቆይቷል። የበጋ ስንዴ መስኖ ልማቱ ዘንድሮ በሁሉም ክልሎች ላይ እየተካሄደ ይገኛል።

ከግብርና ሚኒስቴር በተገኘው መረጃ መሠረት የዘንድሮ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት አዝመራ ስብሰባ አዝመራው አስቀድሞ ከደረሰበት የቆላማው አካባቢ በመነሳት በስፋት እየተካሄደ ይገኛል። በደጋና በወይናደጋ አካባቢዎች የሚካሄደው የአዝመራ ስብሰባ ሥራም አሁን በአካባቢዎቹ እየጣለ ካለው ዝናብ አኳያ ሊዘገይ ቢችልም በተቀናጀ መልኩ በርብርብ የሚፈጸም ይሆናል።

በዚህ የአዝመራ ስብሰባ በ2016 ዓ/ም በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ከተሸፈነው ሦስት ሚሊየን ሄክታር ማሳ እስከ መጋቢት 23 ቀን 2016 ድረስ በአንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታር ማሳ ላይ የነበረ የስንዴ አዝመራ ተሰብስቧል፤ ከዚህም ከ50 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ስንዴ ወደ ጎተራ ገብቷል።

የአዝመራ ስብሰባውም አርሶ አደሩን በማስተባበር በደቦና በመሳሰሉት እንዲሁም በኮምባይነር እየተፈጸመ ነው። በቀጣይም እንደ እስከ አሁኑ ሁሉ አርሶ አደሩን፣ ሌሎች የግብርናው ዘርፍ ተዋንያንና የሚመለከታቸውን መንግሥታዊ አካላት በማስተባበር የአዝመራ ስብሰባውን ለማጠናከር እየተሠራ ነው።

የበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱ በቆላ፣ በደጋና ወይና ደጋ አካባቢዎች ሁሉ በስፋት እንደመካሄዱ፣ በልማቱም ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በስንዴ ዘር እንደመሸፈኑ የአዝመራ ስብሰባውም ከፍተኛ ርብርብ ማድረግን ይጠይቃል፤ በአዝመራ አሰባሰቡ እየታየ ያለው ርብርብና ውጤት በበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱ በአጠቃላይ እየተከናወነ ያለው ተግባር በጥሩ ሁኔታ እየተፈጸመ መሆኑን ያመለክታል።

ይህን የበጋ መስኖ ስንዴ አዝመራ አሰባሰብ አቅም ገና ባልተሰበሰበው አዝመራ ላይም በማዋል በዕቅዱ የተያዘው የስንዴ ምርት ያለምንም ብክነት እንዲሰበሰብ አጥብቆ መሥራት ያስፈልጋል። በእቅድ ከተያዘው ከ120 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ የተሰበሰበው ከ50 ሚሊዮን በላይ የሚሆነው ነው። እስከ አሁን አዝመራውን ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ ውለው የአዝመራ አሰባሰቡን ውጤታማ ያደረጉትን አርሶ አደሩን የማስተባበርና ሜካናይዜሽንን በስፋት የመጠቀም ተሞክሮዎችን በቀሪው አዝመራ አሰባሰብ ላይ በሚገባ መተግበር ይገባል።

የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ከመምጣቱ በፊት ባለው ተሞክሮ መሠረት ለአዝመራ ስብሰባ ሥራ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ ሲሠራ የቆየው ለመኸር አዝመራ ብቻ ነው። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ የመኸር ወቅት ከፍተኛ መጠን ያለው በዘር የተሸፈነ ማሳ ያለበትና ከፍተኛ ምርት የሚጠበቅበት በመሆኑ ነው። ወቅቱ ደግሞ ዝናብ የሚጥልበት ከሆነ ርብርቡን ከፍተኛ እንዲሆን ሲያደርገው ኖሯል።

በበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱ በዘር የተሸፈነው ማሳ ብዛትና አሁን እየጣለ ያለው ዝናብም በቀጣይ መካሄድ ያለበትን የመስኖ ስንዴ አዝመራ የመሰብሰብ ርብርቡን ከእስከ አሁኑም በላይ ማድረግ አስፈላጊትነትን የግድ ያደርጉታል። ዝናቡ ከፍተኛ ርብርብ ተደርጎበት በለማ የበጋ መስኖ ስንዴ አዝመራ ላይ ምንም አይነት ጉዳት እንዳያስከትል መላውን ሕዝብ አስተባብሮ መሥራት ያስፈልጋል።

በባሕላዊ መንገድ የሚካሄደውን የአዝመራ ስብሰባ በስፋትና በተቀናጀ አግባብ ማካሄዱ እንዳለ ሆኖ፣ በተለያየ አካባቢ የሚገኙ እንደ ኮምባይነር ያሉ የአዝመራ መሰብሰቢያና መውቂያ ማሽኖችን አስተባብሮና አቅናጅቶ መሥራትም ሌላው ሥራውን የበለጠ ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመፈጸም የሚያስችል ተግባር ነው። ይህን ለማድረግ ደግሞ በበጋ መስኖ ልማቱ ብቻ ሳይሆን፣ በመኸር አዝመራ ስብሰባ በተለያዩ አካባቢዎች ያሉ ኮምባይነሮችን አሰባስቦ በማቀናጀት ውጤታማ ተግባር የተከናወነበትን ተሞክሮ መለስ ብሎ መመልከትና መተግበር ይገባል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሜካናይዜሽን በከፍተኛ ሁኔታ ተስፋፍቷል። አርሶ አደሮች በግልም በጋራም የእነዚህ ማሽነሪዎች ባለቤት የሆኑበት ሁኔታ ሰፊ ነው። የግሉ ዘርፍም ማሽነሪዎችን በኪራይ እያቀረበ ያለበት ሁኔታም እንዲሁ ተስፋፍቷል። እነዚህን አቅሞች አቀናጅቶ ሌት ተቀን በመሥራት ለእዚህ አዝመራ ስብሰባ ሥራ መጠቀም በበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱ የተያዘውን እቅድ ለማሳካት ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**

ወርቁ ማሩ

Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የጎበጠውን የዜጎች ወገብ የሚያቀና አዋጅ

ዳንኤል ዘነበ

በከተሞች አካባቢ የሚታየው የመኖሪያ ቤቶች ዋጋ (ሽያጭም ሆነ ኪራይ) መናር የዜጎች ፈተና እየሆነ ከመጣ ሰንብቷል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ምክንያታዊ እና ፍትሐዊ ያልሆኑ የቤት ኪራይ ጭማሪዎች እየተባባሱ መጥተዋል። በቅርቡ በዓለም ዙሪያ የኑሮ ደረጃዎችን የሚከታተለው ነምቤኦ (NUMBEO) የተባለ ድርጅት በ2024 በአፍሪካ ሀገራት ያለውን የመኖሪያ ቤቶች ዋጋ ዝርዝር ሪፖርት በድረ-ገጹ አውጥቶ ነበር።

በዚሁ ድርጅት መረጃ መሠረት ኢትዮጵያ በመኖሪያ ቤት ዋጋ ውድነት ከአፍሪካ 2ኛ፤ ከዓለም ደግሞ 3ኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች። ዜጎች ለመኖሪያ ቤት የሚያወጡት ዋጋ ከሚያገኙት ገቢ 43 ነጥብ 1 በመቶውን እንደሚሸፍንም ይኸው ድርጅት አስታወቋል። ይህም በሀገራችን የመኖሪያ ቤት ኪራይ መጨመር እጅግ አሳሳቢ እየሆነ መምጣቱን ያመላክታል።

በተለይ ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ ችግሩ ጎልቶ የሚታይ ሲሆን የኑሮ ውድነትን በማባባስ ረገድ ድርብ ፈተናን ፈጥሯል። በዋናነት በዝቅተኛ ገቢ የሚተዳደሩ የከተማዋ ነዋሪዎች ላይ ከፍተኛ ቅሬታ እያስነሳ እና ዜጎችም ተረጋግተው ኑሯቸውን እንዳይመሩ እያደረገ ይገኛል። ተከራይ ለቤት ኪራይ የሚያወጣው ክፍያ ከ30 በመቶ መብለጥ እንደሌለበት የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ይናገራሉ።

አዲስ አበባ ውስጥ ተቀጣሪ ሠራተኞች ከገቢያቸው እስከ 70 በመቶውን፤ አልፎ አልፎምም ሙሉ ገቢያቸውን ለቤት ኪራይ ያወጣሉ። ይህም በመዲናችን አዲስ አበባ የችግሩ ጥልቀትና አሳሳቢነት እስከምን ድረስ እንደሆነ ጠቋሚ ነው። በእርግጥ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የችግሩን አሳሳቢነት ተገንዝቦ ጊዜያዊ መፍትሔ ለማበጀት ሞክሮም እንደነበር አይዘነጋም።

ከተማ አስተዳደሩ ባለፉት ጊዜያት መንግሥት ለችግሩ እልባት ለመስጠት የኪራይ ጭማሪ እገዳ ማድረጉ ይታወቃል። ይሁንና አከራዮች ያለአግባብ የዋጋ ጭማሪ ከማድረግ አልተቆጠቡም። ደንቡ በአግባቡ ተፈጻሚ መሆን ባለመቻሉ፤ መንግሥት ለችግሩ ጊዜያዊ መፍትሔ ለመስጠት ያደረገው ሙከራ የተሳካ አልነበረም።

ዘርፉ በሕግ የሚመራ አለመሆኑ ችግሩ ስር ሰዶ ከቁጥጥር ውጭ እንዲሆን እንዳደረገው ይታመናል። የአከራይ እና ተከራይን መብት ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ማስጓዝ አልቻለም። ስለዚህ ችግሩን ለመቅረፍ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም።

> ዘርፉ በሕግ የሚመራ አለመሆኑ ችግሩ ስር ሰዶ ከቁጥጥር ውጭ እንዲሆን እንዳደረገው ይታመናል። የአከራይ እና ተከራይን መብት ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ማስጓዝ አልቻለም። ስለዚህ ችግሩን ለመቅረፍ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም

በመሆኑም መንግሥት ጣልቃ ገብቶ የመኖሪያ ቤት የኪራይ ዋጋ መናርን ለማስተካከል፣ የቤት ኪራይ ውል በሕግ እንዲመራ ለማድረግ የሚያስችለውንና በአከራይና ተከራይ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን አዋጅ መጋቢት 24 ቀን 2016 ዓ.ም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፀድቋል። የመኖሪያ ቤት ኪራይ ቁጥጥር እና አስተዳደር አዋጅ ከአውሮፓ ጀርመን፣ ከኤስያ ቻይና፣ ከአፍሪካ ኬንያ ሕጉን ለማውጣት ልምድ የተወሰደባቸው ሀገራት መሆናቸውም ታውቋል።

የአዋጁ መፅደቅ ዘርፈ ብዙ ፋይዳ እንደሚኖረውም መረዳት ይቻላል። በአዋጁ መሠረት ማንኛውም የመኖሪያ ቤት ተከራይ እስከ ሁለት ዓመት የመከራየት መብት ተሰጥቶታል። ይህም የመኖሪያ ቤት አከራዮች ይቋቋማሉ በተባሉ "ተቆጣጣሪ አካላት" በዓመት አንድ ጊዜ በሚሰጡት የኪራይ ተመን ዋጋው የሚመራ ሲሆን፤ ይህም የዘፈቀደ የኪራይ ዋጋ ጭማሪን ያስቀራል ተብሏል።

ከዚህ በፊት አከራዮች በፈለጉት ጊዜ ዋጋ ይጨምሩ ነበር። በአዲሱ አዋጅ መሠረት ግን አከራይ የቤት ኪራይ ዋጋ ጭማሪ ማድረግ የሚችለው ተቆጣጣሪው አካል የሚወስነውን ውሳኔ መሠረት በማድረግ ነው።

የመኖሪያ ቤት ኪራይ ቁጥጥርና አስተዳደር አዋጅ ምክንያታዊ ያልሆነ የቤት ኪራይ ዋጋ ጭማሪ እንዳይኖር፣ ሕገ ወጥ የደላላ ጣልቃ ገብነትን በመቀነስ የኑሮ ውድነቱን በተወሰነ ደረጃ ማርገብ ይችላል ተብሎ ይጠበቃል።

ስለዚህ መንግሥት አዋጁን ማውጣቱ በዜጎች ላይ የሚደርሰውን የኑሮ ጫና፤ በተለይ በመኖሪያ ቤት ላይ ያለአግባብ የሚደረገውን የኪራይ ጭማሪ በማስቀረት ዘላቂ መፍትሔ መስጠት ያስችላል። ስለሆነም የአዋጁ መውጣት ለሕዝብ ትልቅ እፎይታን ይፈጥራል፤ በተወሰነ መልኩም ለኑሮ ጫናው ዘላቂ መፍትሔ ያስገኛል ተብሎም ይጠበቃል።

በቀጣይ ከአዋጁ ተፈፃሚነት ጋር ተያይዞ ከወዲሁ ሊታሰብባቸው የሚገቡ ጉዳዮች አሉ። አዋጁ በወረቀት ላይ እንዳይቀር ከወዲሁ ከአተገባበሩ ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግን ያስፈልጋል። ብዙዎች ተስፋ ያደረጉበት ይህ አዋጅ የሚፈለገውን ውጤት እንዲያመጣ በአተገባበሩ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ የግድ ይሆናል።

በአጠቃላይ፣ የመኖሪያ ቤት ኪራይ ቁጥጥር እና አስተዳደር አዋጅ መፅደቅ ግልጽነት፣ ተጠያቂነት፣ ወጥነት እና ተገማችነት ያለው፤ እንዲሁም፣ የአከራይ እና የተከራይን መብት ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ለማስተዳደርና ዘርፉን በሕግ ለመምራት ያስችላል። ነገር ግን ከአዋጁ ተፈፃሚነት ጋር ተያይዞ በትኩረት መሥራት እና ለብልሹ አሠራር ክፍት እንዳይሆን ጥብቅ ክትትል ማድረግም ያስፈልጋል።

# በክልሉ ዘንድሮ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር አንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ችግኞች ይተከላሉ

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡ በአማራ ክልል በዘንድሮ ክረምት በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር አንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ችግኞች እንደሚተከሉ የክልሉ ግብርና ቢሮ ገለጸ።

በአማራ ክልል ግብርና ቢሮ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃ እና አጠቃቀም ዳይሬክተር አቶ ዘላለም ምሕረት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ በዘንድሮ ክረምት በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር በአጠቃላይ አንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ችግኞች ለመትከል ታቅዶ ዝግጅቶች እየተደረጉ ነው።

እስከ አሁን ድረስ ከ280 ሚሊዮን በላይ ለቆጠራ የደረሱ ችግኞች የተዘጋጁ ሲሆን ከተዘጋጁት ችግኞች 42 ነጥብ ሁለት በመቶ አገር በቀል ዝርያዎች መሆናቸውን ጠቅሰዋል። የችግኝ ዝግጅቱ ሚያዚያ ወር መጨረሻ ድረስ ይጠናቀቃል ተብሎ እንደሚጠበቅም ገልፀዋል።

ችግኝ ከመፈላቱ በፊት አስቀድሞ የተከላ ቦታ የመለየት ሥራ መሠራቱን የተናገሩት ዳይሬክተሩ፤ በአጠቃላይ ከታቀደው 221ሺ. ሄክታር በላይ የተከላ ቦታ እስከ አሁን ድረስ ከ117ሺ. ሄክታር በላይ ቦታ መለየቱን ተናግረዋል።

በዘንድሮ ክረምት በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ለመትከል ከታቀዱት ችግኞች 18 ነጥብ አምስት ሚሊዮን የሚሆኑት የአቮካዶ፣ ማንጎና ሌሎች ፍራፍሬዎች መሆናቸውን ጠቁመው፤ እስከ አሁን ወደ 11 ሚሊዮን የሚጠጉ የፍራፍሬ ችግኞች መዘጋጀታቸውን ጠቅሰዋል።

በክልሉ በአብዛኛው ተከላ የሚጀመረው በሰኔ ወር መጨረሻ ወይም በሐምሌ ወር መጀመሪያ መሆኑን አስታውሰው፤ በዘንድሮ ዓመትም እንደዝናቡ ሁኔታ የሚወሰን ሆኖ በእቅድ ደረጃ በተመሳሳይ ጊዜ መያዙን ተናግረዋል።

ባለፈው ዓመት የተተከሉ ችግኞችን የመንከባከብ ሥራዎች መሠራታቸውንና የመጀመሪያው ዙር የፅድቀት ምጣኔ 91 በመቶ መሆኑን ገልጸዋል። በቀጣይ ሁለተኛው ዙር የፅድቀት ምጣኔ ታይቶ ለዕድሳት ተከላ ችግኞች እንደሚዘጋጁ ጠቁመዋል።

ለአረንጓዴ ዐሻራ እየተዘጋጁ ያሉ ችግኞች ውሃ በበቂ መጠን አግኝተው ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲዘጋጁ ባለሙያዎች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት አለባቸው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ አርሶ አደሩም የሚተክልበትን ቦታ አዘጋጅቶ መጠበቅ እንዳለበት ጠቁመዋል።

# “ድርጅቱ በቅንጅት ባለመሥራቱ ከአንድ ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ አጥቷል”

-የመንግሥት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

# “ችግሩ በሁለቱ ድርጅቶች መገፋፋት የመጣ አይደለም”

- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ከባለድርሻ አካላት ጋር በዋናነትም ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጋር በቅንጅት ባለመሥራቱ ከአንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ ማጣቱን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አስታወቀ። ድርጅቱ በበኩሉ ችግሩ በሁለቱ ተቋማት መገፋፋት የመጣ አለመሆኑን ገልጿል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የ2014/15 በጀት ዓመት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የኃይል ማስተላለፊያ መስመሮችና ማከፋፈያ ጣቢያዎች ፕሮጀክት አፈጻጸም የክዋኔ ኦዲት ሪፖርትን በትላትናው እለት ገምግሟል።

በወቅቱ የቋሚ ኮሚቴው ዋና ሰብሳቢ የሺእመቤት ደምሴ እንደገለጹት፤ ድርጅቱ የኃይል ማስተላለፊያ መስመሮችንና ማከፋፈያ ጣቢያ ፕሮጀክት መሠረተ ልማት ዝርጋታና የኃይል ደራሽነትን ለማረጋገጥ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመሥራት የሚያስችል ወጥ የሆነ ሥርዓት እንዳልዘረጋ በሪፖርቱ ተቀምጧል።

ኃይል ሲቋረጥ በድርጅቱ እና በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት መካከል ኃላፊነት ወስዶ ችግሮችን በጋራ ለመቅረፍ በእቅድ ላይ የተመሠረተ ሥራ አልተሠራም ያሉት ሰብሳቢዋ፤ በዚህም ከአገልግሎቱ ጋር በቅንጅት ባለመሥራቱ እና የኤሌክትሪክ ኃይል ለሀገር ውስጥ እና ለጎረቤት ሀገሮች ባለመሸጡ በአማካኝ አንድ ቢሊዮን 271 ሚሊዮን 244 ሺህ 977 ብር ድርጅቱ ማጣቱን በ2013 ዓመታዊ ሪፖርት የተገለጸ መሆኑ በኦዲት ሪፖርቱ ተመላክቷል ሲሉ ተናግረዋል ።


የሺእመቤት ደምሴ


ኢንጂነር አሸብር ባልቻ

ሰብሳቢዋ፤ እነዚህ ተቋማት እንደ ሀገር ትልቅ ኃላፊነት የተሰጣቸውና እንደ አንድ የሚታዩ መሆናቸውን ገልጸው፤ ሆኖም በሁለቱ ተቋማት መገፋፋት ምክንያት ሀገሪቱ ማግኘት ያለባትን ገቢ ማጣቷን ተናግረዋል። ለዚህም ድርጅቶቹ ምንም አይነት የሕግ ማዕቀፍ በሌለው መንገድ መሥራታቸው ምክንያት ነው ብለዋል ።

በቀጣይ በሕግ የታሠረ በስምምነት ሰነድ የተደገፈ ቅንጅታዊ አሠራር በአስቸኳይ በመመሥረት ወደ ሥራ መግባት ይኖርባቸዋል ሲሉ አሳስበዋል ።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ዋና ሥራ አስፈጻሚ ኢንጂነር አሸብር ባልቻ በበኩላቸው፤ ድርጅቱ ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጋር በተለያዩ ጊዜያት በመገናኘት የእቅድም ሆነ የኦፕሬሽን ሥራዎችን በቅንጅት ተወያይቶ ይሠራል ።

ነገር ግን ቋሚነት ያለው የተፈረመ ሰነድ በሁለቱ ድርጅቶች መካከል የለም ሲሉ ገልጸው፤ ይህም እንደ ክፍተት የሚወሰድ ይሆናል ብለዋል ።

ከዚህ በፊት የነበረው ችግር አሁን ላይ እየተቀረፈ ይገኛል ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ ችግሩ በሁለቱ ተቋማት መገፋፋት የመጣ አይደለም ሲሉ አፅንዖት ሰጥተው አስረድተዋል።

በተጨማሪም ድርጅቱ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር እንዲሁም ከክልሎች ጋር በጥሩ ግንኙነት እየተሠራ እንደሚገኝ የተናገሩት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ በቀጣይ በጀት ዓመት ያሉትን ክፍተቶች በማስተካከልና የሕግ ማዕቀፎችን በማዘጋጀት የቅንጅት ሥራውን ለማጠናከር ጥረት ይደረጋል ሲሉ ገልጸዋል ።

# ድጋፉ ማዕከሉ ያለበትን ዋነኛ የትራንስፖርት ችግር የሚቀርፍ ነው

**ማሕሴት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ለመቄዶኒያ የአረጋውያንና አዕምሮ ሕሙማን መርጃ ማዕከል ያደረገው የተሽከርካሪ ድጋፍ ማዕከሉ ያለበትን ዋነኛ የትራንስፖርት ችግር የሚቀርፍ መሆኑ ተገለጸ።

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ለመቄዶኒያ የአረጋውያንና አዕምሮ ሕሙማን መርጃ ማዕከል 3 ነጥብ 8 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ የቢሮ ቁሳቁስ እና 11 ተሽከርካሪዎችን በትናንትናው እለት ድጋፍ አድርጓል።

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ጫልቱ ሳኒ ድጋፉን ባስረከቡበት ወቅት እንደገለጹት፣ ማዕከሉ ሃይማኖት፣ ብሔር፣ ቋንቋ ሳይለይ ከትንሽ እስከ ትልቅ ያቀፈ ትንሽዋን ኢትዮጵያን የምናይበት ትልቅ ማዕከል ነው።

በተለይም ለሀገር ትልቅ ውለታ የዋሉ አረጋውያንን ማገዝና ውለታ መመለስ የሁሉም ኃላፊነትና የእድሜ ዘመን በረከት የሚያሰጥ ነው ብለዋል።

በዚህም ያለልዩነት አንድነትን በማጠናከር በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ለተለያዩ ችግሮች የተጋለጡና እርዳታን ከሚሹ ወገኖች ጋር መደጋገፍ ይገባል ብለው፤ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር የሚያደርገውን ድጋፍን



አጠናክሮ እንደሚቀጥል ሚኒስትሯ አስታውቀዋል።

የመቄዶኒያ የአረጋውያንና አዕምሮ ሕሙማን መርጃ ማዕከል መሥራችና ሥራ አስኪያጅ ቢኒያም በለጠ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ሚኒስቴሩ ላደረገው ድጋፍ አመስግነው፤ ድጋፉ በተለይም የማዕከሉን የትራንስፖርት እጥረት የሚፈታ ነው ብለዋል።

እንደ ቢኒያም (ዶ/ር) ገለጻ፤ በማዕከሉ የሚገኙ በቀን እስከ 100 የሚሆኑ ተገልጋዮች ወደ ሕክምና ቦታ መሄድ አለባቸው። እነሱንም በአብዛኛዎቹ አልጋ ቁራኛ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ በትራንስፖርት እጥረት ምክንያት ወደ ሕክምና ቦታ ለመውሰድም ሆነ ማንቀሳቀስ ሲቸገር ቆይቷል።

አሁን ላይ የተደረገው ድጋፍም ያጋጥም የነበረውን የትራንስፖርት እጥረት በመፍታት አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት ያስችላል ብለዋል።

በማዕከሉ በ26 ቅርንጫፎች 7 ሺህ 500 አረጋውያንና የአዕምሮ ሕሙማን እንደሚገኙ ገልጸው፤ በቀጣይም ቅርንጫፎችን ወደ 120 በማሳደግ ከ20 ሺህ በላይ ድጋፍ የሚሹ ዜጎችን ለመጨመር የተያዘውን እቅድም የሚያሳካ መሆኑንም አስታውቀዋል።

በመሆኑም ሁሉም የማኅበረሰብ ክፍል ሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ ያደረገውን መልካም ተግባር አርዓያ በማድረግ የተቸገሩትን ለመርዳት የድርሻውን መወጣት አለበት ብለዋል።

ማዕከሉን በአካል በመምጣት ወይም በ8161 አጭር የጽሑፍ መልዕክት በመላክ እንዲሁም የቁሳቁስና የተለያዩ በዓላትን በጋራ በማዕከሉ በማክበር፣ በሙያዊ ድጋፎች እና ለማዕከሉ በማንኛውም መልኩ የሚደረገው ድጋፍ አጠናክሮ እንዲቀጥልም ቢኒያም (ዶ/ር )ጥሪ አቅርቧል።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## ስመነሻ የንግድ ስራ የፈጠራ ሀሳቦች ድጋፍ እያደረገ የሚገኘው ማዕከል

**ወርቅነሽ ደምሰው**

በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ ዘመኑን የዋጁ ጉልበት፣ ጊዜ እና ወጪ የሚቆጥቡ፣ ይበልጥ ምርታማ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ከምንም ጊዜ በላይ እንደ አሸን እየፈሉ እንዲሁም እየተስፋፉ ናቸው፤ እነዚህ ቴክኖሎጂዎች በኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽንና ቴክኖሎጂ (በአይሲቲ) ዘርፍ የሚሰሩ ሲሆኑ፣ በምርምርና በፈጠራ ሥራዎች ላይ ትኩረት በማድረግ የተሰሩ ስለመሆናቸው ብዙ አስረጂዎችን መጥቀስ ይቻላል።

ቴክኖሎጂዎቹ ችግር ፈቺ፣ የሰውን ልጆች የዕለት ተዕለት ሕይወት የሚያቀሉ፣ ለአጠቃቀም ቀላል እና ምቹ እንዲሁም የተለያዩ አማራጮች ያላቸውም ናቸው። በዚህም ረገድ የሚሰሩ የፈጠራና የምርምር ሥራዎች እየተበራከቱ እና እያደጉ መምጣቸውን የዘርፉ ባለሙያዎች በመጥቀስ፣ ሥራዎቹ እንዲስፋፉ ምቹ ምህዳር በመፍጠር የምርምርና የፈጠራ ሀሳብ ያላቸው ሰዎችን ማበረታትንና መደገፍን እንደሚጠይቅ ያስገነዝባሉ።

በኢትዮጵያም በአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው የአስር ዓመት የልማት እቅድ የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽንና ቴክኖሎጂ (የአይሲቲ) ዘርፍ ትኩረት ተሰጥቶት ዲጅታላይዜሽን ለማስፋፋት የሚያስችሉ በርካታ ሥራዎች እየተሰሩ ናቸው፤ ይህን ተከትሎም ለውጦች የተመዘገቡባቸው ሁኔታዎች መኖራቸውን መረጃዎች ያመላክታሉ። የፈጠራ ሀሳብ ላላቸውና ለባለልዩ ተሰጥኦ ሰዎች ትኩረት በመስጠት ለየት ያሉ ማዕከላት በማቋቋም ለማበረታታትና ለመደገፍ የሚያስችሉ ሥራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ።

በቅርቡም የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ከኮርያ ዓለም አቀፍ ትብብር ኮይኮ /KOICA/ ጋር በመተባበር በኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽንና ቴክኖሎጂ (በአይሲቲ) ዘርፍ መነሻ የንግድ ስራ ፈጠራ ሀሳቦች (startups) ያላቸውን ለማበረታታት እና ለመደገፍ የሚያስችል የኢኖቬሽን ማዕከል በመገንባት አስመርቋል።

ማዕከሉ በኢትዮጵያ አይሲቲ ፓርክ የተገነባ ሲሆን፣ ‹‹ኢኖቢዝ-ኬ ኢትዮጵያ›› “Innobiz-K Ethiopia Center” የሚል ስያሜም ተሰጥቶታል። ኢኖቢዝ-ኬ ኢትዮጵያ ማዕከል የቢዝነስ እና የቴክኒክ ስልጠና፣ ፕሮቶታይፖችን የማዘጋጃ ማሽኖች፤ ለመነሻ የንግድ ስራ ፈጠራ ሀሳቦች (startups) ቢሮ፣ የጋራ መስሪያ ቦታ፣ የቢዝነስ ሴንተር እና የቢዝነስ ትስስር ሥራዎችን ለመስራት የሚያስችሉ ስፍራዎችን የያዘ ነው። ማዕከሉ ፈጠራን በማጎልበት፣ መነሻ የንግድ ስራ ፈጠራ ሀሳቦች ያላቸውን /ስታርታፖችን/ በማብቃት እና የኢኮኖሚ እድገትን በማፋጠን ረገድ ትልቅ ምዕራፍ ይከፍታል ተብሎ የታመነበት ነው።

የ‹‹ኢኖቢዝ-ኬ ኢትዮጵያ›› የኢኖቬሽን ማዕከል ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሰላምይሁን አደፍርስ እንዳሉት፤ የማዕከሉ መገንባት የማህበረሰብ ችግሮች የሚፈቱ ቁልፍ ሀሳቦች የሚመነጩበትንና ሊያድጉ የሚችሉበትን ስነምህዳር መፍጠርን ያለመ ነው። ማዕከሉ ፈጠራን የሚያዳብር፣ ምርምርንና ልማትን የሚያበረታታ የፈጠራ ጅምሮች እና ኢንተርፕራይዞችን እድገት የሚደግፍ ምቹ አካባቢ ለመፍጠር ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ለመሆኑ አንዱ ማሳያ ነው።

በኢኖቬሽን ዘርፍ ያሉ የፈጠራ ሀሳቦች በተለየ መልኩ ጥንቃቄ ይፈልጋሉ። መነሻ የንግድ ስራ ፈጠራ ሀሳቦች (startups) አስፈላጊና የተቀናጁ ድጋፎችን እንደሚፈልጉ አቶ ሰላምይሁን ይናገራሉ። ማዕከሉም መነሻ የንግድ ስራ ፈጠራ ሀሳብ (startups) ያላቸውን አንድ ላይ በማሰባሰብ እርስ በርስ የሚረዳዱበትንና የሚደጋገፉበትን ምቹ የሥራ ከባቢ ለመፍጠር እንደሚረዳም ይገልጻሉ። ይህ ምህዳር /ኢኮ ሲስተም/ ምቹ የሥራ ከባቢ ከመፍጠሩም ባሻገር በትስስር ለመፍጠር እንደሚያግዝ ያመላክታሉ። ቀደም ሲል ብዙ ጊዜ እንደዚህ አይነት የሥራ ከባቢዎች የሚፈጠሩት በኢንቨስተሮች፣ በዩኒቨርሲቲዎች እና በኢንዱስትሪዎች አማካኝነት መሆኑን ጠቅሰው፤ እነርሱም የፈጠራ ሀሳብ ያላቸው እየተሳሰሩና እየተደጋገፉ የሚሄዱባቸው ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያደረጉ እንደነበር አስታውሰዋል።

‹‹የዲጅታል ሲስተሙ ከሚፈልጋቸው መሠረተ ልማቶች አንዱ የፈጠራ ሀሳብ ያላቸውን የሚያበረታቱና የሚደግፉ ማዕከላትን ማስፋፋት ነው ››ያሉት አቶ ሰላም ይሁን፤ ‹‹የዚህ ማዕከል መገንባት ብቻ በቂ አይደለም። ብዙ እንደዚህ አይነት ማዕከላትን በከተሞችና በክልሎች ማስፋፋት ያስፈልጋል። ለዚህም ገና ብዙ ሥራ መስራት ይጠበቅብናል ›› ብለዋል።

ማዕከሉ እንደ ሀገር ትልቅ ፋይዳ እንዳለው ጠቁመው፤ መነሻ የፈጠራ ሀሳብ ያላቸው ወጣቶች ሀሳባቸው ላይ ኢንቨስት እንዲያደርጉ እና ትልልቅ ንግዶችን እየፈጠሩ ችግሮችን ሊፈቱ የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች እውን እንዲያደርጉ ማስቻል እንደሚገባ ተናግረዋል።

ማዕከሉ ኢንኩቤሽን ማዕከላት ማሟላት ያለባቸውን ሁሉንም ነገሮች አሟልቶ የያዘ ነው ያሉት አቶ ሰላም ይሁን፤ ዘመኑን የዋጁ ሥራዎችን መስራት የሚያስችሉ ማሽኖች እንዳሉትም ጠቁመዋል። በጋራ የሚሰራባቸው ምቹ የሥራ ከባቢዎች፣ ሞዴል (prototype) የሚሰራባቸው ቦታዎች እና ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ቢሮዎች፣ የመዝናኛ ቦታዎች፣ የሕጻናት ማቆያ እና ሌሎች መሰል ሥራዎች የሚሰራባቸው ቦታዎች ማካተቱንም አመላክተዋል።

እንደ አቶ ሰላም ይሁን ማብራሪያ፤ በማእከሉ የፈጠራ ሀሳብ ያላቸውን በማወዳደር ብቃት ያለው ሀሳብ ያላቸው ወደ ማዕከሉ እንዲገቡ በማድረግ ስልጠናና የተለያዩ ድጋፎች እንዲያገኙ ይደረጋል። የፈጠራ ሀሳብ ሲባል ዝም ብሎ ሀሳብ ያለው ሳይሆን ለየት ያለ የኢኖቬሽን ሀሳብ ያለውን የሚያመላክት ነው። ኢኖቬሽን ስንል አንድ ሀሳብ ከሀሳብነት ተነስቶ ወደ ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ አስተዋጽኦ የሚሸጋገር አዲስ ሀሳብ ነው። ሀሳቡ የማይሸጋገር ከሆነ ሀሳቡ ብቁ ወይም ጊዜውን የጠበቀ አይደለም ማለት ነው።

‹‹ማንኛቸውም ሀሳብ ያላቸው ሰዎች ይወዳደራሉ። ሀሳባቸው ተወዳድሮ የሚመጥንና ብቁ ሆኖ ከተገኘ አሸንፎ ይወጣል›› የሚሉት አቶ ሰላም ይሁን፤ ሀሳባቸው አሸንፎ ወደ ማዕከሉ የሚገቡትም የሚደረግላቸው ድጋፍ በአንድ ጊዜ የሚያቆም ብቻ ሳይሆን ተከታታይነት ያለውና እያደገ የሚመጣ እንደሚሆን ያመላክታሉ። አሁን ዋናው ነገር መሆን ያለበት ስነ ምህዳሩን /ኢኮሲስተሙን/ መፍጠር መሆኑን ጠቅሰው፤ ስነ ምህዳሩ እየሰፋ በሄደ ቁጥር የሰዎች የመፍጠር አቅማቸው እየጨመረ እንደሚመጣ አመላክተዋል።

ከዚህ በተጨማሪ በዘርፉ በርካታ ሥራዎች እየተሰሩ መሆናቸውን የጠቆሙት አቶ ሰላም ይሁን፤ ‹‹ኢኖቬሽን ለልማት›› በሚል መሪ ሀሳብ ከኮይካ እና ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት የልማት ፕሮግራም/ ዩኤንዲፒ/ ጋር በመተባባር እየተሰራ መሆኑን ይገልጻሉ። የማዕከሉ ሥራ በዚህ የሚያበቃ እንዳልሆነ ገልጸው፣ ለስራው ቀጣይነት በጋራ እንደሚሰራም ገልጸዋል፤ ማዕከሉ የሚያስፈልጉት የአይሲቲ መድረኮች (platforms) እንዳሉ ይጠቁማሉ። አገሪቷን የሚወክል አንዱ የመረጃ ሥርዓት እንዲኖር ለማድረግ ትልቅ ሥራ እየተሰራ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ሰላም ይሁን፤ አጠቃላይ ኢኮ ሲስተሙን የሚወክል የመረጃ ሥርዓት እንዲኖር ለማድረግ እየተሰራ ያለው ሥራ ሲጠናቀቅ የተሻለ ኢኮ ሲስተም እንደሚፈጠር አስረድተዋል።

**ኢኖቢዝ-ኬ ኢትዮጵያ ማዕከል የቢዝነስ እና የቴክኒክ ስልጠና፣ ፕሮቶታይፖችን የማዘጋጃ ማሽኖች፤ ስመነሻ የንግድ ስራ ፈጠራ ሀሳቦች (startups) ቢሮ፣ የጋራ መስሪያ ቦታ፣ የቢዝነስ ሴንተር እና የቢዝነስ ትስስር ሥራዎችን ስመስራት የሚያስችሉ ስፍራዎችን አካቶ የያዘ ነው**

የኢኖቢዝ-ኬ ኢትዮጵያ ማዕከል የሜከር ስፔስና አይሲቲ ዩኒት አስተባባሪ ወጣት ታምራት ተከለ ማርቆስ በበኩሉ ማዕከሉ የኢኖቬሽን ፈጠራ ሀሳብ ያላቸው የሥራ ፈጣሪዎች ሀሳባቸውን ወደ ንግድ ለመቀየር እንደሚረዳቸው ይናገራል።

ታምራት እንደሚለው፤ ማዕከሉ ለመነሻ የንግድ ስራ ፈጠራ ሀሳቦች (startups) ሞዴል (prototype) ለመስራት የሚያግዙ ዘመናዊ ማሽኖችና ቁሳቁስ ተሟልተውለታል። የፈጠራ ሀሳብ ያላቸውን ሀሳባቸውን ይዘው ወደ ማዕከሉ ሲመጡ ሀሳባቸውን ወደ ተግባር በመለወጥ ወደሚታይ ነገር ለመቀየር የሚጠቀሙባቸው ዘመናዊ ማሽኖችም አሉት። ዘመናዊ ማሽኖቹ የፈጠራ ሀሳባቸውን እውን የሚያደርጉበት ሞዴል (prototype) ለመስራት የሚያግዙ 3ዲ ፕሪንተሮችን ጨምሮ እጅግ ዘመናዊ ማሽኖች ተገጥመውለታል።

‹‹ ማዕከሉ የፈጠራ ሀሳብ ላላቸውና ሀሳባቸውን እውን ለማድረግ ምቹ ከባቢና ድጋፍ ላጡ ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል›› ሲል ታምራት ይናገራል፤ አንድ የመነሻ የንግድ ስራ ፈጠራ ሀሳብ (startups) በንድፍ ያለውን ሀሳቡን ወደሚፈልገው ተጨባጭ ነገር ለመቀየር ማሽኖች እንደሚያስፈልጉት ጠቅሶ፤ እነዚህን ማሽኖች ማግኘት ካልቻለ ግን ሀሳቡ ሀሳብ ብቻ ሆኖ ከግብ ሳይደርስ ይቀራል ይላል። እነዚህን ማሽኖች መጠቀም የሚችልባቸው አጋጣሚዎች ከተፈጠሩለት በሀሳቡ ሞዴል (prototype) መስራት ይችላል ሲል ያስረዳል።

መነሻ የንግድ ስራ ፈጠራ ሀሳብ (startups) ያላቸውና የማዕከሉ ተጠቃሚ መሆን የሚፈልጉ ሁሉ የማእከሉን ስልጠናዎችንና የተለያዩ ድጋፎችን ያገኛሉ። ይህ ብቻ አይደለም፤ በተለይ ዘመናዊ ማሽኖች በተገጠሙለት ክፍል ውስጥ የሚሰሩት ዋንኛ ሥራ ሀሳባቸውን እውን አድርገው ወደ ንግድ ከመለወጣቸው በፊት ሀሳባቸውን በሞዴል (prototype) አውጥተው በማየት ማስተካከል ያለበት ነገር ካለ እንዲያስተካክሉ እና ሌሎችም አስተያየት እንዲሰጡበት ለማድረግ እንደሚያግዛቸው ይገልጻል። ሀሳባቸው እውን የሚሆንበት በሞዴል (prototype) ማውጣት የሚችሉበት እንደሆነ ያስረዳል።

ዘመናዊ ማሽኖቹ የፈጠራ ሀሳብ እና ሥራው ተቀባይነት አግኝቶ ወደ ንግድ ተቀይሮ ለገበያ በሚውልበት ጊዜም ለመጠቀም የሚገለግሉባቸውና የሥራ እድልም ለመፍጠር የሚያስችሉ መሆናቸውን ታምራት ይገልጻል፤ ከሁሉም ቅድሚያ የሚሰጠው ግን ወደ ማዕከሉ የሚመጣ መነሻ የፈጠራ ሀሳብ (startups) ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ላይ ያተኮረ የፈጠራ ሀሳብ ሆኖ ተወዳድሮ አሸናፊ ሊሆን የሚችል ሀሳብ መሆን እንዳለበት አብራርቷል።

እንደ ታምራት ማብራሪያ፤ የኢኖቢዝ-ኬ ኢትዮጵያ ማዕከል ዋና ዓላማ የንግድ ፈጠራ ሀሳብ ያላቸው ወደ ማዕከሉ ገብተው ሀሳባቸው እውን እንዲሆን ከሀሳብ ተነስተው ወደ ገበያ እስከሚገቡ ድረስ ስልጠና አግኝተው፣ የፈጠራ ሀሳቡን ወደ ሥራ እንዲቀይሩ ማስቻል ነው። ለዚህም ማዕከሉ አስፈላጊውንና ተከታታይነት ያለው ድጋፍ ያደርጋል።

እስካሁን ማዕከሉ በሙከራ ደረጃ ሀሳብ ያላቸውን በስድስት ዙር አወዳድሮ አሸናፊዎቹን ተቀብሎ ስልጠና በመስጠት እና የተለያዩ ድጋፎች በማድረግ ሀሳቦች እውን እንዲያደርጉ እገዛ ሲያደርግ መቆየቱን አስታውሷል። ሀሳቦች ነጥረው በመውጣት ለአገር ኢኮኖሚም አስተዋፆኦ የሚያበረክቱት የፈጠራ ሀሳብ ያላቸው ሁሉ ሀሳባቸውን ወደ ንግድ የሚቀይሩበት ሁኔታ ሲኖር መሆኑን ይገልጻሉ። ማዕከሉ የፈጠራው ባለቤቶች ሀሳባቸውን ይዘው ሲመጡ ወደ ተግባር እንዲገቡ በሁሉም ረገድ እገዛ እንደሚያደርግ አስታውቋል።

‹‹ከዩኒቨርሲቲ በተለያዩ ሙያዎች ተመርቀው ለተግባር ልምምድ (internship) መውጣት የሚፈልጉ ተማሪዎች ማዕከሉን መጠቀም ይችላሉ›› የሚለው ታምራት፤ የፈጠራ ሀሳብ ያላቸው ሀሳባቸው እውን እንዲሆን የሚፈልጉ ወጣቶች በማንኛውም ጊዜ ወደ ማዕከሉ በመምጣት መስራት ይችላሉ ሲልም ጠቁሟል። ማዕከሉም ለእነዚህ አካላት ሰልጠና በመስጠት፣ ቴክኒካዊ እና የተለያዩ ድጋፎች በማድረግ አብሮ በመስራት ዓላማቸውን እንዲያሳኩ እንደሚያደርግ ገልጾ፤ ትክክለኛ የፈጠራ ሀሳብ ያላቸው ሀሳባቸውን ይዘው ወደ ማዕከሉ ቢመጡ እነርሱም ተጠቅመው አገርም ይጠቅማሉ ሲል አስገንዝቧል።

በተለይ ኢኖቬሽን ላይ ትኩረት ያደረጉ አዳዲስ መነሻ የፈጠራ ሀሳቦች ያላቸውና ማዕከሉ የሚያወጣቸውን የመወዳደሪያ መስፈርቶች የሚያሟሉ ሁሉ መወዳዳር እንደሚችሉ ጠቅሶ፣ በመስፈርቱ መሰረት ሀሳባቸው አሸናፊ የሆነ ወደ ማዕከሉ ገብተው ተጠቃሚ መሆን እንደሚችሉ አመልክቷል። አቶ ታምራት ሀሳብ ያላቸው አካላት እንዲወዳደሩም ጥሪ አቅርቧል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# መርካቶ ያበቀላት ጠንካራ ሰራተኛ

አስመረት ብስራት

የመርካቶ ስም ሲነሳ ዋና መጠቅለያዋ ሆኖ የሚያገለግለን “አራዳነት” የሚለው ቃል ነው። አንዳንዶች “የመርካቶ ልጅ ቀልጣፋና ጨላጣ ነው!” ይሉታል። ሌሎች ደግሞ የመርካቶ ልጅ “ቢዝነስ ሁሌም በእጁ ነው” ለማለት ሲሹ፤ “የመርካቶ ልጅ ጦሙን አያድርም” ይላሉ።

አንዳንዶች ደግሞ ፍጥነቱና አዋቂነቱ እያስደመማቸው፤ “የመርካቶ ልጅ ከጨበጥክ በኋላ የእጅህን ጣቶች መጉደል አለመጉደላቸውን ቁጠር” ይላሉ። በሥልጡንነቱና በዕውቀቱ እንዲሁም በልምዱ የሚኮሩት ደግሞ፤ የመርካቶ ልጅ ቱሪስትና ፒስኮር ከለየ የቆየ፣ “ጨውና አሞሌ፣ ወመንቴና አለሌ ገና ዱሮ አንጥሮ ያየ”፣ የዕውቀት ሰው ነው እያሉ፣ በእርግጠኝነት ይናገራሉ።

የመርካቶ ልጅ፤ ንግድን ከሕይወቱ ጋር ያዋሃደና ልምዱን ለነገ ማዋል የሚችል፣ አወንታዊ ልዕልና ያለው የተግባር ሰው ነው፤ ብለው የሚናገሩ አያሌ ናቸው። ጣሊያን “መርካቶ እንዲጂኖ” የሚለን፤ ሠፈውን የምስራቅ አፍሪቃ ገበያ የራሱ የሆነ ልዩ ባህሪ ያለው ነው ሲለን ነው። ሌሎች ፈረንጆች “The indigenous Merkato” እንደሚሉት መሆኑ ነው።

መርካቶ ከምስራቅ አፍሪካ አንደኛ ሰፊ ገበያ ነው። የመርካቶ ትልቁ አዳራሽ፤ በበላይ ተክሉ ኬክ ቤት፣ በዋንዛ ካፍቴሪያ፣ በዋርካ ካፍቴሪያና በሰሜን ሻይ ቤት፣ እንዲሁም ወደ አራተኛ ሲል ባለው በምስራች ሆቴል እና በበርካታ ልብስ ሱቆች የተከበበና የታጀበ ነው።

ነገርን ነገር ያነሳዋል እንዲሉ ስለ መርካቶ ያነሳሁት መርካቶ ተወልዳ ያደገች፤ በባልትና ውጤቶች ንግድ የተሰማራች፤ በንግዱም ዓለም ገብታ ስኬታማ የሆነች እውነትም የመርካቶ ልጅ የምታስብልን ፈጣን የንግድ ሰው የሆነች ሴትን ላስተዋውቃችሁ ስለወደድኩ ነው። መልካም ቆይታ።

ገነት ብርሃኑ ትባላለች። ተወልዳ ያደገችው መርካቶ አውቶብስ ተራ አካባቢ ሲሆን አሁን አዲስ አበባ ሳሪስ አካባቢ ትኖራለች። ባለ ትዳርና የሶስት ልጆች እናት ስትሆን ልጆቿን አሳድጋ የእሷን እርዳታ መፈለግ ባቆሙበት ወቅት ነበር ሁልጊዜ የምትመኘውን የባልትና ስራን ለመስራት የተነሳችው።

"ባልትና ስራን የመረጥኩት የውስጥ ፍላጎት ስላለኝ ነው" የምትለው ወይዘሮ ገነት ሰው የውስጥን ፍላጎት አዳምጦ ሲሰራ ስኬታማ ይሆናል ብላ እንደምታስብ ትናገራለች።

ለቤተሰቦቿ ሶስተኛ ልጅ ስትሆን ወላጆቿ ከወለዷቸው ሶስት ልጆች በጠጨማሪ የቤተሰብ ልጆች ቤት ሞልተው ያሳድጉ ነበር። ወላጆቿ ቤት እንግዳ የማይጠፋበት የእንግዳ ተቀባዮች ቤት ነበር። ቤቱ የበርካቶች ማረፊያ፤ የብዙዎች ሕይወት ማደላደያ፤ መሸጋገሪያ የሆነ ቤት ውስጥ እንዳደገች ትናገራለች። እንዲህ በደግነት የተሞላ ቤት ውስጥ ያደገችው ሴት እራሷም በዛ የቤተሰብ ስርዓት እየተመራች ኑሮዋን እየመራች መሆኑን ታብራራለች።

"ልጆቼ አድገው ትምህርት ቤት ሲገቡ ነው የወጣሁት። ልጅ ድሪያለሁ የመጨረሻ ልጄ አስር ዓመቱ እያለ ነው ሰራ የገባሁት ቁጭ ማለት አልፈለኩም። ከእራሴ አልፌ ለሌሎች የስራ እድል ልፈጥር ብዬ ነው። "ብላለች።

በዚህ ሁኔታ ያደገችው ሴት የእራሷን ቤት መስርታ በመልካም የእናትነት ሰርዓት ልጆቿን አሳድጋለች። ልጆቿ እራሳቸውን ማስተዳደር በሚችሉበት እድሜ የእራሷን ስራ የምትሰራበትን ሀሳብ ይዛ ተነሳች።

### የንግድ መነሻ ካፒታል

የባልትና ውጤትን እያዘጋጁ ለገበያ ማቅረብ የሚለውን ሀሳቧን እውን ለማድረግ መነሻ ካፒታል ማፈላለግ ጀመረች። ከጥቃቅንና አነስተኛ ለስራ የሚሆን ሶስት መቶ ሺ ብር ብድር ያገኘችው ይች ሴት በተለያየ ጊዜ በወሰደችው ስልጠና መሰረት በግል የሚተዳደር የባልትና ውጤቶች ማምረቻ አቋቋመች። የግለሰብ ነጋዴ የሚተዳደር የንግድ ቤት በርካታ ጥቅሞች እንዳሉት የምትናገረው ወይዘሮ ገነት ከጥቅሞቹም መካከል የድርጅቱ ባለቤት በድርጅቱ አጠቃላይ እንቅስቃሴ ብቸኛ ውሳኔ ሰጭ የሆነበት ነው። የግል ድርጅቶች አብዛኛውን ጊዜ ብዙ ካፒታልና ሙያዊ የሆነ እውቀት የማይጠይቁ ሥራዎች ላይ ሰዎች በቀላሉ የንግድ ፈቃድ አውጥተው የራሳቸውን የንግድ ሥራ የሚመሰርቱበት አደረጃጀት መሆኑም ሌላው ጥቅም ነው ትላለች። በመሆኑም ስትደራጅ ለብቻዋ ተበድራ ለመስራት መምረጧን ትናገራለች።



ፎቶ በረሁን

ወ/ሮ ገነት ብርሃኑ

> **ሰው ስሜቱን ተከትሎ መስራት ከጀመረ ስኬት ደጁ ላይ መሆኑን ማመን አለበት**

በአንድ ግለሰብ የሚመሰረቱ የንግድ ድርጅቶች ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ጥቅሞች ይኖሩታል የምትለው ወይዘሮ ገነት በዚህ መልኩ ዝርዝር ሁኔታውን አስቀምጣለች። በግለሰብ የሚቋቋም ንግድ በቀላሉ የሚመሰረት መሆኑ ማለትም የዚህ አይነት የንግድ ድርጅት ለመመስረት ከሌሎች ሰዎች ጋር መሻረክ፣ የጋራ ስምምነት ላይ መድረስ ወዘተ. የማይጠይቅና ሙሉ በሙሉ በግለሰቡ ውሳኔ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ሂደቱን ቀላል የያደርገዋል። አንድ ግለሰብ በፈለገው ሙያ፣ በፈለገው ጊዜና ቦታ ንግዱን የመመስረት ሙሉ ነፃነት አለው።

በአነስተኛ ካፒታል ይመሰረታል መመስረቱም ሌላው መሆኑን የምታስረዳው ወይዘሮ ገነት የዚህ አይነት የንግድ ድርጅት ለመመስረት የሚያስፈልገውን የካፒታል መጠን የሚወስን ሕግ ባይኖርም ግለሰቡ የመረጠውን የንግድ ሥራ ማስኬድ እስከቻለ ድረስ አነስተኛ በሆነ ካፒታል ሊመሰረት ይችላል።

የንግድ ሥራው ብቸኛ ተጠቃሚ ባለቤቱ መሆኑን የምትናገረው ወይዘሮ ገነት የንግድ ሥራው የሚመራውና የሚተዳደረው በአንድ ግለሰብ እንደ መሆኑ በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚገኘውን ጥቅምም እንዲሁ ብቸኛ ተጠቃሚ ይሄው ግለሰብ ይሆናል ማለት ነው።

ድርጅቱን የመምራት ነፃነት የእሯሷ መሆኑን ጠቅሳ የንግድ ድርጅቱን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ማለትም ድርጅቱን የመምራት፣ የማስፋፋት ካልፈለገም ደግሞ የማፍረስ ወይም የመዝጋት፣ ሰራተኛ የመቅጠር ወይም የማሰናበት ውሳኔዎችን ያለማንም ጣልቃ ገብነት ባለቤቱ ብቻውን የመወሰን ሙሉ ነፃነት አለው ትላለች።

ሌላው የንግድ ሚስጥር ከመጠበቅ አኳያ የግል ድርጅት ጥቅም አለው። ማለትም አጠቃላይ የንግድ እንቅስቃሴው የሚመራው በአንድ ግለሰብ እንደ መሆኑ ለንግድ ስራው ጠቃሚ ናቸው የሚባሉና የሚስጥር መያዝ ያለባቸው ጉዳዮች በራሱ በባለቤቱ ብቻ የተያዙ በመሆናቸው ከራሱ ፈቃድ ውጭ በሆነ መንገድ ሊባክኑ አይችሉም ይህ ማለት ደግሞ ብራንድን በብቸኝነት ለመጠበቅ ልዩ ጥቅም አለው ብላለች።

ግብር ከመክፈል አኳያ የተሻለ ጥቅም አለው የምትለው ወይዘሮ ገነት በአንድ ግለሰብ የሚመራ የንግድ ድርጅት ግብር የሚከፍለው አንድ ጊዜ ብቻ በመሆኑ በግብር አከፋፈል ረገድ ተጠቃሚ ነው ትላለች።

### የስራ ሂደትና ጥረት

ስራውን ስትጀምር ሶስት ቋሚ ሰራተኞችን ይዛ መነሷቷን ትናገራለች። አሁን ላይ እንደ ጊዜውና ሁኔታው በኮንትራት የሚቀጠሩ ሰዎች መኖራቸውንና አሁን አምስት ቋሚ ሰራተኞች መኖራቸውን ታስረዳለች።

የኮንትራት ሰራተኞች የሚቀጠሩት ምርት በብዛት ሲታዘዝ ሲሆን ለእነዚህ ጊዚያዊ ሰራተኞች ከሶስት ሺህ እስከ አምስት ሺህ ብር ድረስ በወር የሚከፈል ይሆናል ብላለች። ለቋሚ ሰራተኞችም ተመሳሳይ አይነት የክፍያ ስርዓት ሲኖር ቋሚዎቹ ከመደበኛ የስራ ጊዜያቸው ውጪ የሰሩበትም የሚከፈላቸው መሆኑን ታብራራለች።

"ስራ ለመጀመር የተነሳሁት በራሴ ቦታ ላይ ነበር " የምትለው ወይዘሮ ገነት የማምረቻም የመሸጫም ሱቅ እዛው መኖሪያ ቤቷ አካባቢ አድርጋ ከፍ ወዳለ ስኬት ጉዞ ጀመረች። የባልትና ውጤቶቿን ቤቷ ባለው ሱቅ ከመሸጥ አልፋ በአላትን እየተከተሉ የሚዘጋጁ ባዛሮች ላይ ይዛ መውጣት ጀመረች።

ምርት እየበዛ ደንበኞቿ የባልትና ውጤቶቿን ጣእም እየለዩትና እየመረጡት ሲመጡ ቤቷ ካለው ሱቅ በተጨማሪ ብዙ ደንበኞች ወደምታገኝበት ቦታ ሱቅ ተከራይታ መስራት ጀመረች። ከአንድ የሰፈር ውስጥ ሱቅ ከፍ ወዳለ ደረጃ የተሸጋገረችው ይች ሴት በሞራል ለስኬት መታተር ጀመረች።

የባልትና ውጤቶች ሲባል ከበርበሬ አንስቶ ሽሮ፤ በሶ፤ ቅመማ ቅመም፤ የአጥሚት እህል፤ ቆሎ በስራው ከሚቀርቡት መካከል ሲሆን ማንም ሰው ጉልበት የሚጠይቀውን ይህን ጥራቱን የጠበቀ የባልትና ውጤቶች በቀላሉ ከሱቅ አንስቶ እንዲጠቀም ማድረጓን በኩራት ትናገራለች።

የገበያ ሁኔታ በየወቅቱ የሚለያይ መሆኑን የምትናገረው ወይዘሮ ገነት "በየወቅቱ የገበያውን ሁኔታ እየተከተሉ የሚመጡት የተለያዩ አይነት ፍላጎቶች እንደየ ፍላጎቶቹ እያመረትን እንሸጣለን " ብላለች። ዋና የገበያ ጊዜ በዓላትን አስታኮ የሚከፈቱ ባዛሮች መሆናቸውን ተናግራ ብዛት ያለው ምርት በዚህ ወቅት እንደሚሸጥ አስረድታለች።

### ስኬት

በሶስት መቶ ሺ ብር ብድር ስራ ለመጀመር የተነሳችው ይቺ ሴት አሁን ላይ ብድሯን መልሳ አምስት መቶ ሺ ብር ተቀማጭ ገንዘብ አላት። ከዛም በተጨማሪ የሚንቀሳቀስ ገንዘብና የመስሪያ ማሽኖች፤ የምርት ግብአቶች፤ ተመርተው ያልተሸጡ ምርቶች ተጫማምሮበት የተሻለ የሚባል አቅም መፍጠሯን ትናገራለች።

"ገነት ባልትና ልዩነቱ ጥራቱ ነው " የምትለው ወይዘሮ ገነት፤ ይህን በጥንቃቄና በጥራት የሚመረት የባልትና ወጤት በቀጣይ የታወቀ ብራንድ የማድረግ ሕልም እንዳላት ትናገራለች። በቀጣይ በጥራቱ የታወቀ የባልትና ብራንድን በመያዝ ሱፐር ማርኬቶች ውስጥ በመግባት አማራጭ ሆና ለመቅረብ እየሰራች መሆኑን ታብራራለች።

ባለቤቴ በስራው ላይ ድጋፍ ከሚሰጡኝ ሰዎች አንዱ ነው የምትለው ወይዘሮ ገነት፤ ግብኣት ከማቅረብ አንስቶ ሽያጭ ላይ በመሳተፍ ልጆቼም አብረው ይሰራሉ ትላለች።

### በመጨረሻም

ሰዎች ስራ ከመጀመራቸው በፊት ውጤታማ እሆናለሁ ወይ? የነፍሴ ጥሪ ነው ወይ? የምወደውን ስራ ነው ወይስ የምሰራው ?የሚያጋጥሙኝን መሰናክሎች በስኬት እወጣዋለሁ ወይ? የሚለውን አስቦ ወደስራ መግባት ይኖርበታል። ሰው ስሜቱን ተከትሎ መስራት ከጀመረ ስኬት ደጁ ላይ መሆኑን ማመን አለበት ትለናለች። እኛም ሰው ከተሰማራ እንደየስሜቱ በዋለበት ሜዳ አይቀርም ማፍራቱ ብለን ተሰናበትናችሁ። ቸር ይግጠመን።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

የዛሬው አዲስ ዘመን ድሮ ወደ 1966 ዓ.ም ላይ ማረፊያው አድርጋል። ከየአቅጣጫው አመጾች ተስፋፍተው በነበሩበት በዚያ ጊዜ የሠራተኛው እንቅስቃሴ፤ ሁለቱ ኢትዮጵያውያኑ አውሮፕላን ጠላፊ ባልና ሚስት በኢንቴቤ፤ ከአራቱ ሚስቶቹ ሦስቱን በአንድ ጊዜ ስለፈቱት የአፍሪካ መሪ እንዲሁም ሆዳሞች ተብለው ከሥራቸው ስለተባረሩት ሁለት ሠራተኞች የወጡ ዘገባዎች ያስታውሰናል።

### የሠራተኛ እንቅስቃሴ

ቁጥራቸው ከ90 ሺህ በላይ የሆነው የኢትዮጵያ ሠራተኞች አንድነት ማኅበር አባሎች፤ በኢትዮጵያ ሲደረግ የመጀመሪያ የሆነው የ4 ቀን ጠቅላላ የሥራ ማቆም አድማ ካደረጉ በኋላ፤ በዚህ ሳምንት በሙሉ ሥራቸውን ጀምረዋል። የኢትዮጵያ ሠራተኞች አንድነት ማኅበር አባሎች የ4 ቀን ሥራ ማቆም አድማ ያደረጉት የኑሮ ውድነት ወደ 60 በመቶ ከፍ በማለቱ ተመጣጣኝ የደመወዝ ጭማሪ እንዲደረግላቸውና አንዳንድ የመሻሻል ለውጥ እንዲደረግ ለመጠየቅ ነበር። ሠራተኞች ሥራ ባቆሙበት አራት ቀን ውስጥ በነሱ ተወካዮችና በመንግሥት፤ እንዲሁም ከምክር ቤት በተውጣጣ ቡድን መካከል የተደረገ ንግግር ሠራተኞች በጠየቋቸው 17 ጉዳዮች፤ በየደረጃ በሥራ እንዲውሉ የሚመለከት ስምምነት ተደርጓል።

...

የሲቪል አቪዬሽን መሥሪያ ቤት ሠራተኞች የአበል ጭማሪን፤ የሕይወት ዋስትናን፤ የማኅበር ማቋቋምና የቋሚ ሠራተኛነትን መብት ጥያቄ አመልክተው የሥራ ማቆም አድማ በማድረጋቸው፤ በኢትዮጵያ አየር ላይ የነበሩ የውጪ አገር ኤሮፕላኖች እንዳይገቡ አድርጓል።

...

መምህራን ቀደም ሲል የጀመሩት የሥራ ማቆም አድማ እንደቀጠለ ነው።

**(አዲስ ዘመን መጋቢት 6 ቀን 1966 ዓ.ም)**

### አውሮፕላን የጠለፈው ኢትዮጵያዊ ታወቀ

ባለፈው ረቡዕ ንብረትነቱ የምሥራቅ አፍሪካ አየር መንገድ የሆነ ፎክነር ፍሬንድሺፕ ፒ.ኤፍ.57 የተባለ ኤሮፕላን ከኬንያ ዋና ከተማ ናይሮቢ ወደ ማሊንዲ 30 መንገደኞችንና አራት የኤሮፕላን ሠራተኞችን ይዞ በሚበርበት ወቅት በኢትዮጵያውያን ባልና ሚስት ተጠልፎ ዑጋንዳ ውስጥ ኢንቴቤ ኤሮፕላን ማረፊያ ነዳጅ ለመሙላት እንዳረፈ፤ በጉዳዩ ጄኔራል ኢዲ አሚን ጣልቃ ገብተው ኢትዮጵያዊው ጠላፊ ከነባለቤቱ እጁን መስጠቱ መገለጡ ይታወሳል።

ይህንኑ የሚመለከተውን ጉዳይ ኢስት አፍሪካን ስታንዳርድ የተባለው ጋዜጣ በዝርዝር አውጥቶታል። በጋዜጣው እንደተመለከተው፤ አቶ ከሡት የተባለ ኢትዮጵያዊና ባለቤቱ ኤሮፕላኑን የጠለፉት፤ ከናይሮቢ ወደ ማሊንድ በበረራ ፕሮግራሙ መሠረት ተነሥቶ የ15 ደቂቃ በረራ እንዳደረገ ነው። ኢትዮጵያውያኑ ባልና ሚስት የኤሮፕላኑን ሠራተኞች በሽጉጥ ካስፈራሩ በኋላ የኤሮፕላን ነጂ አቅጣጫውን ለውጦ ወደ ሊቢያ እንዲበር አለዚያ ግን እንደሚገደል ጠላፊዎቹ ነግረው የኤሮፕላኑን ነጂ ካፒቴን ፔንፎልድ ጉዞውን ወደ ሊቢያ ከመቀጠሉ በፊት ነዳጅ ለመጨመር ዑጋንዳ ውስጥ ኢንቴቤ ኤሮፕላን ማረፊያ አረፈ። የምሥራቅ አፍሪካ አየር መንገድ ባለሥልጣኖች የዑጋንዳ ባለሥልጣኖች ርምጃ ለመውሰድ ጣልቃ እንዳይገቡ ቢጠይቁም፤ የዑጋንዳው ፕሬዚዳንት አሚን በአስቸኳይ ወደ ሥፍራው ሔደው ጠላፊውን በማነጋገር ከነባለቤቱ እጃቸውን እንዲሠጡ ለማግባባት መቻላቸውን ጋዜጣው አመልክቷል።

ኢትዮጵያዊው መምህርና ባለቤቱ ኤሮፕላኑ ለጊዜው ወደ ሊቢያ እንዲበር አስገደዱት እንጂ ለመሔድ ያሰቡት ወደ ሞስኮ እንደነበር በጋዜጣው ተጠቅሷል። ጄኔራል አሚን ጠላፊዎቹን አግባብተው እጃቸውን እንዲሰጡ ካደረጉ በኋላ ከተሳፋሪዎቹና ከኤሮፕላኑ ሠራተኞች ጋር ምሳ ተጋብዘዋል።

ከአዲስ አበባ መጣሁ የሚለው ከሡት ያልተስተካከለ እንግሊዘኛ መናገር የሚችል ሲሆን ስሟ ያልተጠቀሰው ባለቤቱ ግን፤ የምትናገረው አማርኛ ብቻ መሆኑን ጋዜጣው ገልጧል። መምህር ነኝ የሚለው ከሡት ኤሮፕላን የጠለፈው ሀገሩ አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ ስለምትገኝ ከዚሁ ለመራቅ በማሰብ መሆኑን ገልጧል።

**(አዲስ ዘመን የካቲት 9 ቀን 1966ዓ.ም)**

### ፕሬዚዳንት አሚን ከአራት ሚስቶቻቸው ሦስቱን ፈቱ

ካምፓላ፤ የዑጋንዳው ፕሬዚዳንት አሚን ከአራቱ ሚስቶቻቸው መካከል ሦስቱን እንደፈቱና የፈቱበትን (ሰማንያ ያወረዱበትን) ምክንያት ለዑጋንዳ ሚኒስትሮች ምክር ቤት አባሎች ያብራሩ መሆናቸው ተገለጠ። ጀኔራል አሚን የፈቷቸው ኬይ፤ ኖራና፤ ማማ ማሪያም የተባሉትን ሲሆን የቀሩት ባለቤታቸው መዲና አሚን የተባሉት ናቸው።

በዜናው እንደተገለጠው አሁን ከተፈቱት የጀኔራል አሚን ባለቤቶች መካከል ኬይ የተባሉት በቅርቡ ባልታወቀ ምክንያት ተገድለው አስከሬናቸው በዓባይ ጅረት ላይ ሲንሳፈፍ የተገኘው የቀድሞው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሌተና ኮሎኔል ማይክል አንዶጋ የቅርብ ዘመድ ሲሆኑ፤ ማማ ማሪያም ደግሞ ባለፈው ዓመት የተሰደዱት የቀድሞው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ዋኑሜ ኪቤዲ ዘመድ መሆናቸው ታውቋል።

እነዚህን ሁለት ሚስቶቻቸውን የፈቱት ከራሳቸው ፍልስፍና ጋር የማይሔድ የንግድ ጥቅም የመሠረቱ በመሆናቸው እንደሆነ ጀኔራል አሚን ገልጠዋል። ሦስተኛ ባለቤታቸውን የፈቱት ግን ከራሳቸው ጋር ዝምድና ስላላቸው ብቻ መሆኑን ገልጠዋል።

...

**(አዲስ ዘመን የካቲት 17 ቀን 1966ዓ.ም)**

### ሆዳሞች ተብለው ከሥራ ተባረሩ

ጃካርታ ፤ በኢንዶኔቪያ ውስጥ በሰሜናዊ ሴሊበስ ደሴት በአንድ የወይን ጠማቂ ፋብሪካ የሚሠሩ ሁለት ሰዎች ከሚፈቀድላቸው በላይ ሩዝ በመመገብ ችግር ስለፈጠሩ ከሥራ መባረራቸውን ሲናር ሃራፖን የተባለው የጃካርታ ጋዜጣ አመልክቷል።

በወይን ጠማቂው ፋብሪካ ውስጥ አሥር ዓመት የሠሩት ሁለት ሰዎች ሆዳሞች ተብለው እንዲባረሩ ምክንያት የሆነው በያንዳንዱ የምግብ ሰዓት እያንዳንዳቸው ሦስት ሦስት ሣህን ሩዝ መብላታቸው ነው።

ሁለቱም ሠራተኞች ከሥራ የመባረራቸውን ሁኔታ ለክፍሉ የሠራተኛ ጉዳይ መሥሪያ ቤት በአቤቱታ መልክ አቅርበው ውጤቱን በመጠባበቅ ላይ መሆናቸውን ጋዜጣው ጨምሮ ገልጧል።

**(አዲስ ዘመን የካቲት 17 ቀን 1966 ዓ.ም)**

# ዓለም አቀፍ

## የቦይንግ አውሮፕላን የሞተር ሽፋን በበረራ ላይ ተገንጥሎ መውደቁ ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የአሜሪካው የሳውዝዌስት አየር መንገድ ንብረት የሆነው ቦይንግ 737-800 አውሮፕላን በበረራ ላይ እያለ የሞተሩ ሽፋን ተገንጥሎ መውደቁ ተነገረ።

ወደ አሜሪካዋ ሁስቶን በረራ ላይ የነበረው አውሮፕላን ችግሩ ማጋጠሙን ተከትሎ ዴንቨር ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ለማረፍ መገደዱ ተነግሯል።

135 መንገደኞችንና 6 የበረራ አባላት ያሳፈረው አውሮፕላን ዴንቨር ለማረፍ ከመገደዱ በፊት 10 ሺህ 300 ጫማ ከፍታ ላይ እየበረረ እንደነበረም ነው የተገለጸው።

ችግሩ ማጋጠሙን ተከትሎ የአሜሪካ የአየር መንገድ ተቆጣጣሪዎች አፋጣኝ ምርመራ እያደረጉ መሆኑም ተነግሯል።

የአሜሪካው የሳውዝዌስት አየር መንገድ በቦይንግ 737-800 አውሮፕላን ላይ ያጋጠመውን ችግር የአየር መንገዱ የጥገና ቡድን እንደሚመረምረው አስታውቀዋል።

አየር መንገዱ ለእንደዚህ አይነት ክፍሎች ጥገና ኃላፊነት እንዳለበት አረጋግጧል።

ቦይንግ ኩባንያ የአሜሪካው የሳውዝዌስት አየር መንገድ በቦይንግ 737-800 አውሮፕላን ላይ ባጋጠመው ችግር ዙሪያ እስካሁን አስተያየት አልሰጠም።


የዓለማችን ግዙፍ የአቪየሽን ኩባንያ የሆነው ቦይንግ ካሳለፍነው ጥር ወር ጀምሮ በ737 ማክስ 9 አውሮፕላን መስኮቱ ተገንጥሎ መውደቁን ተከትሎ ትችቶችን እያስተናገደ ይገኛል።

ከዚህ ጊዜ በኋላ ተደጋጋሚ የምርት ጥራት ችግሮች የተከሰቱ ሲሆን የአሜሪካ አቪዬሽን አስተዳደር በኩባንያው ላይ የቴክኒክ ጥራት ምርመራዎችን አድርጓል።

ኩባንያው በቦይንግ 737 ማክስ 9 አውሮፕላን ምርቶች ላይ ካከናወናቸው 89 የጥራት ምርመራዎች ላይ በ33ቱ ጉድለት እንደተገኘበት መገለጹም ይታወሳል።

ይህ አውሮፕላን በተለይም የኤሮ ሲስተሙ ሲፈተሽ የጥራት ደረጃውን ያሟላው ከ13 ነጥቦች በስድስቱ ብቻ አልፏል ተብሏል።

የኩባንያው የቴክኒክ ባለሙያዎች ስለ 737 ማክስ 9 አውሮፕላን በቂ እውቀት እንዳላቸው በተደረገው ምርመራ የሚገባውን ያህል ያውቃሉ የሚለውን ኩባንያው ማስረዳት እንዳልቻለም ተገልጿል።



## ዩክሬን በዛፖርዥያ የኑክሌር ኃይል ጣቢያ ላይ ያደረሰችው ጥቃት "አደገኛ ትንኮሳ ነው"- ሩሲያ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ሩሲያ ቤተመንግሥት ክሬሚሊን ዩክሬን በሩሲያ ቁጥጥር ስር ባለው የዛፖርዥያ ግዛት በሚገኘው የኑክሌር ኃይል ጣቢያ ላይ ያደረሰችው ጥቃት "በጣም አደገኛ ነው" ሲል ገልጿል።

የክሬሚሊን ቃል አቀባይ ዲሜትሪ ፔስኮቮ "ይህ አደገኛ ትንኮሳ ነው" ብለዋል።

"ይህ በረጅም ጊዜ እጅግ አደገኛ ጉዳት የሚያስከትል ነው። እንዳለመታደል ሆኖ የኪቭ መንግሥት የሽብር ተግባሩን ቀጥሏል" ሲሉ ተናግረዋል ፔስኮቮ።

ሩሲያ ዩክሬን ባለፈው እሁድ እለት በሩሲያ ቁጥጥር ስር ያለውን የዛፖርዥያ ኑክሌር ጣቢያ ሦስት ጊዜ ማጥቃቷን ገልጻ ምዕራባውያን ምላሽ እንዲሰጡ ጠይቃለች።

ነገር ግን ዩክሬን በጥቃቱ እጇ የለበትም ብላለች።

በአውሮፓ ትልቁ የሆነው የኑክሌር ኃይል ማመንጫ ጣቢያ በቁጥጥር ስር የዋለው ሩሲያ በየካቲት 2022 በዩክሬን ላይ ልዩ ያለችውን ወታደራዊ ዘመቻ በከፈተች በጥቂት ወራት ውስጥ ነበር።

ስትጀምር "ልዩ ወታደራዊ ዘመቻ" እያካሄደች መሆኑን ስትገልጽ የነበረ ቢሆንም አሁን ላይ ምዕራባውያን እየተሳተፉ በመሆናቸው ግጭቱን ጦርነት ብላ እየጠራችው ነው።

አራት የዩክሬን ምሥራቃዊ ግዛቶችን በከፊል የያዘችው ሩሲያ ሙሉ በሙሉ እስከምትቆጣጠራቸው ድረስ ማጥቃቷን እንደምትቀጥል መግለጿ ይታወሳል።

በቅርቡ ወሳኝ የተባለችውን አቭዲቪካን ጨምሮ በርካታ መንደሮችን የተቀጣጠረችው ሩሲያ ወደፊት ለመግፋት ጥረት እያደረገች ትገኛለች።

ዩክሬን ወደኋላ ለማፈግፈግ የተገደደችው የምዕራባውያን ወታደራዊ ድጋፍ በፍጥነት ባለመድረሱ ነው፣ አሁንም የማይደርስ ከሆነ ተጨማሪ ቦታዎችን ልትለቅ እንደምትችል እየገለጸች ነው።

ፕሬዚዳንት ዘለንስኪም ሩሲያ እያደረሰችው ያለው ተከታታይ የረጅም ርቀት ሚሳይል ጥቃት ከቀጠለ ዩክሬን የአየር መከላከያ ሚሳይል ሊያልቅባት ይችላል ሲሉ አስጠንቅቀዋል።



## ነፃ ሃሳብ

# የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ጥምረትለኃይል አቅርቦትና ተደራሽነት

**ታምራት ተስፋዬ**

ዓለማችን ካፈራቻቸው ስመጥር የምጣኔ ሃብትና ምሁራን መካከል የሚመደቡት፣ ዴቪድ ሰቴርን፣ ፖል ቡሩክና ስቴቨን ቡሩንስ«The Impact of Electricity on Economic Development: A Macroeconomic Perspective» የሚል የኤሌክትሪክ ኃይል አቅም አቅርቦትና ተደራሽነት ከአንድ አገር ከሁለንተናዊ እድገት ጋር ጥብቅ ቁርኝት እንዳለው በሚያትት የጋራ ጥናታዊ ፅሁፋቸው ይበልጣል ይታወቃሉ። በጥናታቸው፣ «እድገት ሲታሰብ በተለይም የኃይል ዘርፉ ልማት ከሌሎች ስራዎች ቀድሞ በመገኘት ለማክሮ ኢኮኖሚ እድገትን ወሳኝ ሚና መጫወት እንዳለበት» ያሰምሩበታል።

በዚህ እሳቤ ልክና መነፅር ኢትዮጵያን ከተመለከትና ከመዘናት የኃይል ዘርፉ ልማትና የአገሪቱ ጉዞ እኩል መገዝ እንዳልሆነላቸው በቀላሉ መረዳት አንቸገርም። በአሁኑ ወቅት በኢንዱስትሪው፣ በአገልግሎት ዘርፉ እንዲሁም የእያንዳንዱ ግሰለሰብ ቤት የኃይል ፍላጎትና ፍጆቻ በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል።

በአገሪቱ በአሁን ወቅትም አስተማማኝ፣ ጥራቱና ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሁም የማህበራዊና የኢኮኖሚ ልማት ፍላጎት በበቂ ሁኔታ የሚደግፍ የኃይል አቅርቦት አይስተዋልም። የመነጨውን ኃይል ውጤታማ በሆነ መልኩ ተደራሽ ከማድረግ አንፃር ጉልህ ድክመት ስለመኖሩ የሚያከራክር አይደለም።

የኃይል ማስተላለፊያ መስመሮችም በበቂ ሁኔታ ያልተዳረሱ፤ የኃይል ፍላጎቱን በበቂ ሁኔታ መሸከም የማይችሉና በየወቅቱ አስፈላጊው ጥገና ያልተደረገላቸው ናቸው። የኃይል ብክለቱም ልዩ ትኩረት የሚፈልግ ጉዳይ ነው። በዓለም አቀፉ ኢነርጂ ኤጀንሲ ጥናት መሰረት ኢትዮጵያን ጨምሮ በአፍሪካ ከሚመረተው ኃይል ውስጥ ከ20 በመቶው በላይ የሚሆነው ይባክናል። ኢትዮጵያ በዓመት እስከ 350 እስከ 400 ሜጋ ዋት እንደሚባክን ይታመናል። ይህም ብክነቱን ጣና በለስ ግልገል ጊቤ 2 የኃይል ማመንጫ ከሚያመርተው ጋር የሚቀራረብ ነው እንደ ማለት ነው።

የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ እድገት ለማጎልበት በተለይም አገሪቱን ለኢንቨስትመንት ከሚመቹት ተርታ ለማሳለፍ ሙስናን ጨምሮ ሌሎችም መሰናክሎች ከማስወገድ ባሻገር ለኃይል መሰረተ ልማትና ተደራሽነቱ እንዲሁም ብክነቱን ለመከላከል ከፍተኛ ትኩረት መሰጠት የግድ ይላል።

በአሁን ወቅትም መንግስት የኃይል አቅርቦት እጥረትን ለመቅረፍ ሁለንተናዊ ልማቱ የሚጠይቀውን የኃይል ፍላጎት ለማርካት የተለያዩ የኃይድሮ ፓወር ልማት ፕሮጀክቶችን በአገሪቱ ዋና ዋና ወንዞችና ተፋሰሶች ላይ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል።

ከእነዚህ መካከልም በአሁን ወቅትም በፍፃሜ ዋዜማ ላይ የሚገኘውና ከአፍሪካ ቀዳሚ የኃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫዎች አንዱ የሆነው የሕዳሴ ግድብ በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳል። 1 ሺ 870 ሜጋ ዋት ኃይል የሚያመነጨው የጊቤ ሶስት ፕሮጀክትም ሌላኛው ማሳያ ነው።

ይሁንና ኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ልማትና እድገት የሚጠይቀውን ፍላጎት ለማሟላት በተለይም የኃይል አማራጭን ማስፋት ብሎም ውጤታማ በሆነ መልኩ ተደራሽ ለማድረግ የተጀመሩ እርምጃዋን ወደ ሩጫ መቀየር የግድ ይላል። በተለይም የአየር ንብረት ላይ ተፅእኖ የማያሳድሩና ከብክለት ነፃ የሆኑ የኃይል አማራጮቾችን ማስፋት እጅጉን ወሳኝ ነው።

> **የኃይል ምንጭ ስብጥሩን በማስፋት፤ የማስተሳሰፊያና ማሰራጫ መሰረተ ልማትን በማጠናከርና የአሰራር ስርዓቱን በማዘመን የዘርፉን የአገልግሎት ጥራትና አስተማማኝነትን ለማረጋገጥ የግሉ ዘርፉ ተሳትፎ እጅጉን ወሳኝ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም**

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ከፍተኛ የውሃ ሃብት ያላት አገር ናት። የተለያዩ ጥናቶችም የአገሪቱ የኃይድሮ ፓወር አቅም 45 ሺ ሜጋ ዋት ኃይል ማመንጨት የሚያስችል መሆኑን ያሳያሉ። የአገሪቱ ኃይል በአብዛኛው የሚመነጨው ከውሃ ነው። ይሕ ደግሞ አቅርቦቱን ከተፈጥሮ ዘላቂነትና አስተማማኝነት ጋር ያስተሳስረዋል። ከአየር ንብረት ሰላማዊነት ጋር ሕልውናው እንዲጣበቅ ያደርገዋል። እንዴት ከተባለም የአየር ንብረት ለውጥ በተለይ የዝናብ እጥረት፣ የግድቦችን የውሃ መጠን ሲቀንስ ብሎም ሲያደርቅ እንደነበር ማስታወስ በቂ ምላሽ ይሆናል። ከመሰል የአየር ንብረት ተፅእኖ ቅጣት ለማምለጥ ታዲያ ፊትን ወደ ታዳሽ ኃይል ማዞር የግድ ይላል።

የአገሪቱ የኢነርጂ ምርት ከካርቦን ልቀት ነጻ በሆኑ በታዳሽ ኢነርጂ ምንጮች ላይ እንዲመሠረትና በቁጠባ ጥቅም ላይ እንዲውል የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም ተግባራዊ እየተደረገ ባለው የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ስትራቴጂ ውስጥ ዋነኛ ስትራቴጂ ሆኖ ተቀምጧል።

ኢትዮጵያ ታዳሽ የኃይል አማራጮች ሃብታም ናት። በመልክአ ምድራዊ አቀማመጥ ምክንያት ከፍተኛ የፀሃይ ኃይል ማምረት የሚያስችል አቅም አላት። ከነፋስ እና ለእንፋሎት ወይንም ጂኦተርማል ኃይል ያላት እምቅ አቅም እጅግ በጣም ከፍተኛ ስለመሆኑ የተለያዩ ጥናቶች ይመሰክራሉ።

እምቅ የታዳሽ ኃይል ምንጮች ባለቤት እንደመሆኗ መጠን ከዚህ ሀብቷ የራሷን የኢነርጂ ፍላጎት ከማሟላት ባሻገር ቀጠናዊ የኃይል ትስስሩን እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም የውጭ ምንዛሪ ምንጭን ለማሳደግ እንዲሁም የኃይል ዘርፉ በአካባቢው ጂኦፖለቲካዊ መረጋጋት የሚኖረውን ሚና ከፍተኛ እንዲሆን ይታመናል።

የአሁን ወቅትም የኢኮኖሚ ልማት ግቦችን ለማሳካት የኃይል አማራጭን የማስፋትና ያላትን እምቅ አቅም በአግባቡ ለመጠቀም እየተጋች ትገኛለች። የኤሌክትሪክ አቅርቦት እጥረትን ለመፍታትም ከፍተኛ መዋለ ንዋይ ፈሰስ በማድረግ ከተለያዩ የኃይል አማራጮች ማለትም የውሃ፣ ንፋስ፣ እንፋሎትና የፀሐይ ኃይል አማራጮችን እየተመለከተች ትገኛለች።

በአስር ዓመቱ የልማት እቅድም ማለትም በ2030 ዓ.ም የአገሪቱ የኃይል አቅርቦት ፍላጎት እስከ 17 ሺ ሜጋ ዋት በላይ እንደሚደርስ ይጠበቃል። ይሕ ፍላጎት በመንግስት ተሳትፎና ሕዝብን ማእከል ባደረገ መልኩ በራስ አቅም በሚሰበሰብ ገንዘብ የተለያዩ የኃይል መሰረተ ልማቶች ግንባታ ብቻ ምላሽ ያገኛል ተብሎ አይጠበቅም። ይሕ መንገድም ብዙ ርቀት የሚያስኬድ አይደለም።

በኢትዮጵያ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ስንመለከት የኃይል ዘርፉን የማልማት ተግባር መንግስት ከፍተኛውን ድርሻ ይዞ መቆየቱን መታዘብ እንችላለን። የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ እድገት የሚፈልገውን ኃይል ጥማት በማርካትና በማልማት ሂደት በተለይ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ አለ ከማለት የለም ለማለት የማያስደፍር ነው።

ይሁንና የኃይል ምንጭ ስብጥሩን በማስፋት፤ የማስተላለፊያና ማሰራጫ መሰረተ ልማትን በማጠናከርና የአሰራር ስርዓቱን በማዘመን የዘርፉን የአገልግሎት ጥራትና አስተማማኝነትን ለማረጋገጥ የግሉ ዘርፉ ተሳትፎ እጅጉን ወሳኝ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም።

መረጃዎች የሚያመላክቱት፣ በመንግስትና በግሉ ዘርፍ መካከል በኃይል መሰረተ ልማት ላይ ያለው ትብብርና አጋርነት እጅጉን ደካማ መሆኑ ነው። ይሕ ውስንነትም በተለይም ባለፉት ዓመታት የኃይል አቅርቦቱን በማጎልበት ብሎም ተደራሽነቱን ውጤታማ በሆነ መልኩ ከማሳለጥ አንፃር የሚፈለገው ለውጥ እንዳይመጣ ማነቆ ሆኖ ቆይቷል።

በመሆኑም በኤሌክትሪክ ኃይል መሰረተ ልማት እና አቅርቦት ጋር ከሚሰሩ የሶስተኛ ወገን ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት መስራት የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በጋራ መተግበር የግድ ይላል። ይሕም ዘላቂ፣ አስተማማኝና ጥራቱን የጠበቀ የመሰረተ ልማት ለመዘርጋትም ሆነ ያሉትን ለማጎልበት እጅጉን ወሳኝ መሆኑ አጠያያቂ አይሆንም። የለውጡ መንግስትም ይሕ እሳቤ ጠንቅቆ እንደገባው የሚያስመሰክሩ የተለያዩ ተግባራት እያከናወነ ይገኛል።

በተለይም በ2010 ዓም የመንግስትና ግል አጋርነት የሕግ ማዕቀፍ ይፋ መሆኑም የሚታወስ ነው። ውሳኔውም የግል ባለሃብቶች በኃይል ማመንጨትና ማከፋፈል ዘርፍ እንዲሳተፉ ሰፊ እድል ከፍቷል። ይሕ ማእቀፍም የመንግስትና የግል አጋርነት ስምምነት የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማገዝ የሚችሉና በግል ባለሀብቶች ፋይናንስ የሚደረጉ ፕሮጀክቶችን ለማበረታታትና ለመደገፍ የሚያስችል አመቺ ከባቢ እንዲኖር ማድረግ ግልጽነትን፣ ፍትሀዊነትን፣ ቅልጥፍናንና ዘላቂነትን ማበረታታት ታሳቢ ያደረገ ነው።

መረጃዎች እንደሚያመላክቱትም፣ በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እድገቱ የሚፈልገውን የኃይል አቅርቦት ለማሟላት የመንግስትና ግሉ ዘርፍ የትብብር የኢንቨስመንቱ ተሳትፎ ለውጦች እየታየበት ይገኛል። በአሁን ወቅትም ከሃያ የበለጡ በመንግስትና ግሉ ዘርፍ ትብብር የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ በመሆን ላይ ናቸው። የኮርቤቴ ከርስ ምድር እንፋሎት ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክትን ለዚህ ማሳያ ነው።

የአሁን ወቅትም የኢኮኖሚ ልማት ግቦችን ለማሳካት የኃይል አማራጭን የማስፋትና ያላትን እምቅ አቅም በአግባቡ ለመጠቀም በሚደረግ ጥረት በተለይ የታዳሽ ኃይል አማራጭ ወሳኝ መሆኑን በማመን መንግስት በዘርፉ ለሚሰማሩ በርካታ ማበረታቻዎችን ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል። ይሕን ማበረታቻ የተቃደሱ ድርጅቶችና ፕሮጀክቶች እንዳሉም ይታወቃል።

የአንዳንዶቹም ቦታ መረጣና የአዋጭነት ጥናት ተጠናቋል። ስራ የጀመሩ ብሎም ለመጀመር በሚያስችል ተክለ ቁመና ላይ የሚገኙም አሉ። የመንግስትና ግሉ ዘርፍ የትብብር ቦርድ ለተዋናዮቹ ፈቃዱን ሰጥቷል። ለውጦች ካላተደረጉ በስተቀር ቦርዱ ዘጠኝ አባላት ያሉት ሲሆን ሰባት ያህል ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች ሁለቱ ደግሞ ከግል ዘርፉ የተወጣጡ መሆናቸውንም ይታወቃል።

በአጠቃላይ በአሁን ወቅት በተለይም የኃይል ዘርፉ ልማት ከሌሎች ስራዎች ቀድሞ በመገኘት ለማክሮ ኢኮኖሚ እድገትን ወሳኝ ሚና እንዲጫወት የተጀመሩ ጥረቶች ይበል የሚያስብሉ ናቸው። ይሑንና በተለይ የግሉን ዘርፍ ከማሳተፍ አንፃር ተጨማሪ ጥረቶችን ማድረግ እንደሚገባ በግልፅ ይታያል።

በመጪዎቹ ዓመታት ከአገሪቱ ሁለንተናዊ ልማትና እድገት ጋር ተያይዞ ትልቅ መፍጠር የሚያስችሉ እድሎች እንዳሉ እርግጥ ነው። እነዚህ እድሎችም እጅጉን አጓጊና ዘርፈ ብዙ በረከቶችን ይዘው የሚመጡ ናቸው። ይሁንና ከበረከታቸው ለማቋደስ ሰፊ ስራን ይጠይቃሉ።

የኢትዮጵያ ሁለንተናዊ እድገት የሚፈልገውን የኃይል አቅርቦት ከማሟላትና በአግባቡ ተደራሽ ከማድረግ አንፃር ከወዲሁ በልዩ ትኩረት የቤት ስራዎችን መስራት ተገቢ ነው። ከሁሉ በላይ በቅርብ ዓመታት ውስጥ የአገሪቱን የኃይል ጥም የማርካት ግዙፍ አቅም ያለው ታላቁ የሕዳሴ ግድብ ግንባታ ከዳር ማድረስና በዲፕሎማሲው መስክ የተገኘውን ድል ይበልጥ በማስቀጠል ቀጠናው ላይ ያለንን አቅም ይበልጥ ማሳየት እጅግ ወሳኝ ነው።

በተለይ በቅርቡ የሚጠናቀቅና ቀጣይ ዓመታት እውን የሚሆኑ ከፍተኛ አቅም ያላቸው የኃይል አማራጮች እንደ አገር ይዘውት የሚመጡትን ዘርፈ ብዙ እድል ከመጠቀም አንፃር በሰፋፊ የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች ግድቦችን ከደለልና መጤ አረም ዘርያዎች ከመጠበቅ አንስቶ፣ በዘርፉ ላይ ቱሪዝምና ግብርናን ጨምሮ ለመሰማራት ፍላጎት ያላቸው ኢንቨስተሮችን ለማስተናገድ ከወዲሁ እጅን ሰብስቦ ጠንካራ ተቋማትን አደራጅቶ መጠበቅ ያስፈልጋል።

ኢንቨስትመንት በማስፋት፣ የኢኮኖሚ መዋዠቆችን ለመከላከል እንዲሁም የኑሮ ውድነት ፈር ለማስያዝ የኃይል አማራጮች ማስፋት፣ የተጀመሩትን በፍጥነት ማጠናቀቅ እንዲሁም የግሉን ዘርፍ ፊት አውራሪ እያደረጉ መዝለቅ ይበልጡን ሊታሰብበት ይገባል።

እንደየደረጃው ከውጭና የአገር ውስጥ ኢንቨስተሮች ጋር ተቀራርቦ መስራትና ተሳትፏቸውን ማጎልበት የግድ ይላል። ለግሉ ዘርፍ ተሳትፎ መጎልበትም አነቃቂና አዳዲስ ማበረታቻዎችን ተግባራዊ ማድረግ ፈፅሞ መዘንጋት አይኖርበትም።

# ወቅታዊ ትንታኔ

# ሀገራዊ ትርክትን የመገንባት ሂደትና ተግዳሮቶቹ

**እፀገነት አክሊሉ**

ከወራት በፊት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስራውን በጀመረበት ወቅት የኢፌዴሪ ፕሬዚደንት ወይዘሮ ሳህለወርቅ ዘውዴ "መንግስት በ2016 ዓ.ም አሰባሳቢ ትርክት ፈጠራና ስራ ላይ ትኩረት ይደረጋል" ነበር ያሉት። ይህ በእንዲህ እንዳለ እንግዲህ ኢትዮጵያውያን የወል ትርክት አለን ወይ? እንዴትስ ነው በትርክታችን ውስጥ አገራችንን የምናያት የሚለውን በዚህ የትንታኔ ጽሁፋችን የምናይ ይሆናል።

አሰባሳቢ ትርክት እንግዲህ ሁላችንም በኢትዮጵያ ማዕቀፍ ውስጥ እንዳለን ሁሉ በአገራችን ጥላ ስር መሰባሰብ እንደሆነ እንረዳለን። ነገር ግን ይህ እሳቤ ብዙዎች በሚረዱት መንገድ ማለትም ሁሉን ጨፍልቆ አንድ የማድረግ ጉዳይ አለመሆኑን ማወቅ መረዳት ይገባል። አሰባሳቢ ወይም ሀገራዊ ትርክት ኢትዮጵያውያን የተለያዩ ማንነቶቻችን ውበቶቻችን መሆናቸውን በመረዳት እነሱን በአግባቡና በስርዓቱ ተግባራዊ እያደረገን በአብሮነታችን መቀጠል የሚያስችለን ነው።

በኢትዮጵያዊነት ውስጥ በተሰባሰብን መጠን ታሪካችንም እሱን ለማስተላለፍ የምንጠቀምበት ትርክታችንም አንድ እየሆነ መምጣቱም የማይቀር ነው። ከዚህ የተነሳም ኢትዮጵያውያን ከፋፋይ ትርክቶችን በመተው በሕብረ-ብሄራዊ አንድነት ላይ የተመሰረተ የወል ትርክት በመገንባት ሰላምን ማጽናትና የጋራ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ያስፈልገናል የሚባለውም ለዚህ ነው።

የወል ትርክት የአንድን አገር ሕዝብ አብሮነት በማጠናከርና የጋራ አገራዊ ዓላማ ለመሰነቅ ትልቅ አስተዋጽኦ ያለውና የታሪክ ሁነቶችን ጭምር የሚያስተሳስር መሆኑን ብዙ የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ።

የወል ትርክት አብሮነትና አንድነትን የማጠናከር ፋይዳው የላቀ ሲሆን በንኡስ ትርክት ላይ አተኩሮ መስራትና ጽንፍ የረገጠ ትርክት መያዝ ደግሞ የመለያየትና የመከፋፈል ምክንያት ሊሆን እንደሚችልም ይታመናል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ፤ በተለያዩ መድረኮች ባስተላለፉት መልእክት ኢትዮጵያዊያንን በጋራ ሊያስተሳስር የሚችልና አንድነትን የሚያጸና የጋራ የሆነ ታላቅ ትርክት ያስፈልጋል ማለታቸው ይታወሳል።

የወል ትርክትን በመገንባት ሕብረ ብሔራዊ አንድነት፣ የጋራ ተጠቃሚነትና የሀገር ግንባታ መሰረቶችን ማኖር እንደሚገባም አስገንዝበዋል። ከፋፋይ አጀንዳዎች ሰላም እንዳይጸና፣ ልዩነትና ተቃርኖ እንዲበረታ የሚያደርጉ በመሆናቸው ሕዝብን የሚጎዱ ናቸው። በመሆኑም ኢትዮጵያውያን ሕብረ ብሔራዊ አንድነትን የሚያጠናክር የወል እውነትን መሰረት አድርገን መስራት ይገባናል ።

ሐሰተኛ ትርክት በኢትዮጵያውያን መካከል ጥርጣሬና ግጭትን በመፍጠር ሀገር የሚያዳክም ሲሆን ብዝሃነትን ያከበረ የወል ትርክትን መገንባት ደግሞ አገርን አጠናክሮ ወደቀጣይ ምዕራፍ የሚያሻግር ድልድይ ነው።

ይህ በመሆኑም እንደ አገር የተቋቋመው የሰላም ሚኒስቴር የተለያዩ የታሪክ አረዳዶችንና አገላለጾችን ለማቀራረብ ከታሪክ ምሁራን ጋር በትብብር እየሰራ ነው። በዚህም በሕብረተሰቡ ውስጥም ሀሳቡ እንዲሸራሸርና ወደ አንድ ማዕቀፍ መምጣት እንዲቻል ብዙ ጥረቶችን ሲያደርግ እንመለከታለን።

ፍጹም ጠቅላይነትም፤ ፍጹም ነጣጣይነትም ለኢትዮጵያ የማይበጁ በመሆናቸው ሕብረ-ብሔራዊነትን ያከበረ አሰባሳቢ መንገድን መምረጥና መከተል አስፈላጊ መሆኑንም ልብ ማለት ይገባል።

ከታሪካችን፣ ከሕልሞቻችን፣ ከአገራዊ ጥቅሞቻችንና ከእሴቶቻችን የሚመዘዝ የጋራ ማንነት ያለን በመሆኑ ይህንን ማጠናከር ላይ መስራት የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት ከመሆኑም በላይ በተለይም ፓርቲ አደራጅተው ሕዝቡን የሚያነቃንቁ ፖለቲከኞችም ይህን ልብ ሊሉ ይገባል።

በመሆኑም ኢትዮጵያውያን የወል እውነት ላይ የተመሰረተ አገራዊ ትርክት በመገንባት የጋራ ሰላምንና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ መስራት የውዴታ ግዴታችን ነው። የወል እውነት ለሀገር በጋራ በመቆም መስራትን፣ ሉዓላዊነትን፣ ሰላምና አንድነትን የሚያጸና በመሆኑ ለዚህ መልካም ዓላማ በጋራ መስራትም ተገቢና አስፈላጊ ነው።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህር የሆኑት አቶ ሽመልስ ሀይሉ እንደሚሉት በመጀመሪያ አገረ መንግስት ስንል በጠንካራ ምሰሶ ላይ የቆመ የጋራ ስነልቦናና ማንነትን መፍጠር የቻለ ማለት ሲሆን፤ እነዚህን የጋራ ስነልቦናና ፍላጎቶችን ለመመለስ የሚችሉ ተቋማትን ያቆመ ማለት ነው።

እንደ አቶ ሽመልስ ገለጻ የጋራ ማንነት ስንል እንደ አገርና ሕዝብ የሚያስተሳስረን አንድ የሚያደርገን አስተሳሰብ የጋራ ፍላጎትን የያዘ ከመሆኑም በላይ የጋራ ትላንት ዛሬና ነገን የያዘም ሊሆን ይገባል። በዚህ ውስጥም እንደ አገር ሁላችንም በጋራ የምናስታውሰው የጋራ ትውስታ ሲኖረን ነው። ይህ ትውስታችን ደግሞ አያት ቅድመያቶቻችን በጋራ ያኖሩትን፤ ያደረጉትን ፖለቲካዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ውጣውረዶችን የምንጋራበት የጋራ ትውስታ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ የዛሬው ትውልድ በጋራ የሚሰራው እያደረገ ያለው ነገር የጋራ ዛሬ በመሆኑ እነዚህን ሁለቱን ያስተሳሰረ የጋራ ራዕይ ማኖር ማለት ነው፤ የሚሉት አቶ ሽመልስ የትላንቱና የዛሬው በደንብ ተሰናስለው ከሌሉ የጋራ አገረ መንግስት ችግር ውስጥ ይገባል፤ እነዚህ ነገሮች ግን በአግባቡና በስርዓቱ ተሰናስለው መቀጠል ከቻሉ የጋራ የሆነ አገረ መንግስትና ትርክት የመገንባት ስራችን ውጤታማ ይሆናል በማለት ያስረዳሉ።

እነዚህን ለአገረ መንግስት ግንባታ ላቅ ያለ ሚና ያላቸው ነገሮች በአግባቡ ለመገንባት ደግሞ በተለይም በእኛ አገር በጣም ያፈነገጡ ሁለት ሃሳቦች ላይ መስራት ይጠበቅብናል፤ አንደኛው እስከ ዛሬ በመጣንባቸው የአገረ መንግስት ግንባታ ሂደታችን ውስጥ አብረን እንዳልኖርን፤ እንዳልተጋባን፤ እንዳልተዋለድን በፖለቲካ በኦኮኖሚ እንዲሁም በማህበራዊ ዘርፎች ላይ አብረን ብዙ ውጣ ውረዶችን እንዳላሳለፍን በማስመሰልና ዝም ብለን ተበታትነን ነው የኖርነው የሚል የተንሻፈፈ አተያይና ትርክት አለ፤ ይህንን በጣም መግራት ይገባል፤ የትላንት የጋራ ትዝታዎችና ታሪኮች እንዳሉን የሚያሳዩ ብዙ የአብሮነት መገለጫዎች ስላሉን እነሱን አምኖ መቀበል ያስፈልጋል።

ለምሳሌ በኢኮኖሚው ዘርፍ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ከሰሜን እስከ ደቡብ ብቻ በአራቱም ማዕዘን የግንኙነት መስመሮች ነበሩን እነዚህ መስመሮች ደግሞ የሚያሳዩት ኢትዮጵያውያን በጋራ እየነገዱ ማህበራዊ ኑሯቸውን በዛ ውስጥ እየኖሩ በፖለቲካና ወታደራዊ ዘርፍም በተመሳሳይ ጥላትን ድል ለማድረግ ሆ ብለው ሲዘምቱ እንደነበር የሚያሳዩ የጋራ የሆኑ ነገሮች አሉን። እነዚህን የጋራ ስነልቦናዎቻችንን በተዛቡ ትርክቶች ማንሻፈፉ የሚጠቅም ባለመሆኑ እነዚህን ማቃናት ላይ ሁላችንም ተረባርበን መስራት ይገባናል ይላሉ።

ሁለተኛው ደግሞ ኢትዮጵያ ሲባል እንዲሁ መለኮታዊ አድርጎ ማሰብና በኢትዮጵያውያን መካከል የሀይማኖትም፤ የብሔርም ምንም ልዩነት የለም ብሎ ያፈነገጠ ሀሳብም አለ። ነገር ግን ነባራዊው ሁኔታ ይህንን እንደማያሳይ ሁላችንም የምናውቀው ሃቅ ነው የሚሉት አቶ ሽመልስ ኢትዮጵያውያን በጣም ብዙ ልዩነት ያላቸው በሀይማኖት፤ በብሔር፤ በስራ፤ በፖለቲካዊ አመለካከት ቢኖራቸውም እነዚህን ልዩነቶቻቸውን አቻችለውና አዋደው አንድ ሆነው የኖሩ በርካታ የጋራ ትዝታዎችና ትርክቶች ያሏቸው ሕዝቦች መሆናቸውም ሊታወቅ የሚገባው እንደሆነም ነው ያስገነዘቡት።

> **ሐሰተኛ ትርክት በኢትዮጵያውያን መካከል ጥርጣሬና ግጭትን በመፍጠር ሀገር የሚያዳክም ሲሆን ብዝሃነትን ያከበረ የወል ትርክትን መገንባት ደግሞ አገርን አጠናክሮ ወደቀጣይ ምዕራፍ የሚያሻግር ድልድይ ነው**

በመሆኑም አሁን ላይ እነዚህን ሁለቱን አስተሳሰቦች ማስታረቅና ወደመካከል ማምጣትና ትክክለኛውን መንገድ ማሳየት መቻል አለብን። ይህንን ማድረግ ስንችል ብቻ ነው የምንገፈልገውን የጋራ ማንነት መገንባት የምንችለው ይላሉ አቶ ሽመልስ።

የሚገርመው ነገር ይላሉ አቶ ሽመልስ ዛሬም ድረስ በውስጣችን ልዩነቶች አሉ እየተባባልን ጦር እየተማዘዝን እንኳን አንድ የሚያደርጉንን ብዙ የጋራ ማንነቶች እየኖርናቸው ነው። በመሆኑም አገራችን ላይ እንደ ማህበረሰብ የማንስማማባቸው ማህበራዊ ችግሮች በየጊዜው ያጋጥሙናል እንጂ እንደ ሕዝብ የተጣላንባቸው ቂምና ቁርሾ የያዝንባቸው ነገሮች የሉም። ይህ ሲባል ደግሞ የማይመቻቸው ፖለቲከኞችም ብዙ ናቸው። ነገር ግን የአገራችንን ታሪክ መለስ ብለን ማጥናት ከቻልን እስከ ዛሬ ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ብሔር በሌላ ብሔር ላይ ጦርነት ከፍቶ ቁርሾ ውስጥ የገቡበት ነገር አይገኝም።

በጠቅላላው የጋራ ማንነታች እንዲገነባ የቆዩት የእኛነት ትርክቶቻችን ሳይበረዙ ሳይከለሱ ለትውልድ እንዲያልፉ ጠንካራ ስራን መስራት ይጠይቃል የሚሉት አቶ ሽመልስ ሕብረተሰቡ እስከ አሁን የመጣበት የአብሮነት ገመዱ እንዳይላላ ማስተማር እንዲሁም ልዩነትን የሚያራቡት የፖለቲካ ልሂቃን ወደ አንድ ጎራ ሰብሰብ እንዲሉ ማድረግ ያስፈልጋል። ከዛ ሁሉ በላይ ደግሞ የፖለቲካ ገበያው መሪ ተዋናይ የሆኑት የመገናኛ ብዙሃን ከኤዲቶሪያል ፖሊሲያቸው ጀምሮ አንድነትን ወደ መስበኩ መዞርና ትኩረት ማድረግ ይገባቸዋል። የጋራ ትዝታዎች እንዳሉን ማውጣትና በዛ ውስጥ የነበሩ ህጸጾችንም እያሳዩ እውነታውን መቀበል ያስፈልጋል።

ትላንት ስህተት ብቻ ወይንም ደግሞ መልካም ነገሮች ብቻ የተከናወኑበት አይደለም ብለን ማሳየትና ዛሬም በደረስንበት ደረጃ ከእኛ ምን ይጠበቃል በማለት የትላንቱ ስህተት እንዳይደገም የትላንቱ ጥሩ ነገር ደግሞ ተሻሽሎ እንዲቀጥል የሚያደርጉ ስራዎች ላይ ማተኮር ያስፈልጋል ይላሉ አቶ ሽመልስ።

የጋራ ማንነት በመገንባት በኩል ውጤታማ ነንም አይደለንምም ማለት ይቻላል የሚሉት ደግሞ በሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህሩ ዶክተር እምሩ ገመቹ ናቸው።

እንደ ዶክተር እምሩ ገለጻ መሰረታዊ በሆኑ ነገሮች ላይ መስተካከል ያለባቸው ጉዳዮቻችን ብዙ ናቸው፤ አንድ የጋራ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እይታ የለንም ለዚህ ማሳያው ደግሞ በባንዲራ እንኳን የምናደርገው ፍጅት ነው። በመሆኑም እነዚህን ነገሮች ወደመካከል አምጥቶ ውጤት ለማየት ዜጎች በተለያየ መልኩ መነጋገርና መግባባት ላይ መድረስ ይጠበቅባቸዋል።


በሌላ በኩልም ምሁራኖች ትልልቅ የሚባሉት የአገር መሪዎች ችግሩን ተቀብለው ለመፍትሔው የተጠናከረ ስራን መስራት አለባቸው፤ የሚገርመው ነገር አንዳንድ አገሮች አሁን እኛ የገባንበትን አይነት የጋራ ማንነትን የማጣት ችግር ውስጥ ገብተው ነበር፤ ነገር ግን በተጠናከረ ስራ ችግሩን ለማቃለል ችለዋል፤ እኛም እነሱ እንዴት ይህንን ጊዜ አለፉት የሚለውን በሚገባ ማየትና ማጥናት ልምድን ቀምሮ እንደ አገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ተግባር ላይ ማዋል እንደሚያስፈልግም ነው የሚናገሩት።

አገራዊ የሆኑ የጋራ ማንነቶቻችን ላይ ትኩረት አድርገን መስራት አለብን የሚሉት ዶክተር እምሩ በዚሁ መካከል ደግሞ ለምንድን ነው? የጋራ ማንነትን የማጉላት ስራችን ጥላ ያጠላበት የሚለውንም በጥሞና ማየትና መገንዘብ ይገባል። ከዛ ውጪ ግን ይህንን ሃሳብ ብቻ ተቀባይ የሚል ግን ማምጣት እንደሚከብድ መረዳት ያስፈልጋል ይላሉ።

እዚህ ላይ ከፖለቲከኞች ውጪ ምሁራን በጉዳዩ ላይ ሰፋ ያለ ጊዜን ወስደው ቢነጋገሩ ለውጥ የሚመጣ ይመስለኛል የሚሉት ዶክተር እምሩ በመሆኑም ሌሎች አገሮችም በዚህ ሂደት ውስጥ ያለፉ በመሆኑና አሁንም እያለፉ ያሉ ስላሉ ከእነዚህ የምንማረውን ይዘን እስከ አሁን እኛም የምካከርናቸውን ነገሮች አቀናጅተን በመነሳት እንዴት ወደፊት እንሂድ የሚለውን ማስቀመጥ ይገባል ብለዋል።

ሕዝብ አብሮ የሚኖር ነው። የጋራ ማንንቱም የእሱ ነው። በመሆኑ ተወካዮቹ በሰከነ መንፈስ ቁጭ ብለው ፖለቲካዊ እሳቤ ትተውት እንደ ሕዝብ ሆነው ቢነጋገሩ ምናልባት የምንፈልገውን የጋራ ማንነት ግንባታ ለማምጣት እንችላለን በማለት አስረድተዋል።

# ስፖርት



## ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በሳምንቱ መጨረሻ ድል ቀንቷቸዋል

ቦጋለ አበበ

ከትናንት በስቲያ በተለያዩ የዓለም ከተሞች በርካታ የጎዳና ላይ ውድድሮች ሲከናወኑ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በተለይም በሁለት ታላላቅ የማራቶን ውድድሮች ድል ቀንቷቸዋል፡፡ ኢትዮጵያውያን አሸናፊ ከሆኑባቸው ውድድሮች መካከል አንዱ የፓሪስ ማራቶን ሲሆን ሌላኛው የዴጉ ማራቶን ነው፡፡

ከወራት በኋላ ትልቁን የስፖርት መድረክ ኦሊምፒክ በምታስተናግደው የፓሪስ ጎዳናዎች ዓመታዊው የፓሪስ ማራቶን ከትናንት በስቲያ ሲካሄድ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በሁለቱም ፆታ አሸናፊ መሆን ችለዋል፡፡

ከዚህ ቀደም በርካታ ታላላቅ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ባሸነፉበት የፓሪስ ማራቶን ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በሁለቱም ፆታ በበላይነት ሲያጠናቅቁም ከአምስት ዓመት ወዲህ የመጀመሪያ ሆኗል፡፡

የመጀመሪያ የማራቶን ውድድራን ያደረገችው አትሌት መስታወት ፍቅር ርቀቱን በ02:20፡45 በማጠናቀቅ የሴቶቹን ውድድር ስታሸንፍ፣ በተመሳሳይ በወንዶች ሙሉጌታ ኡማ 02፡05፡33 ሰዓት በመግባት ውድድሩን በቀዳሚነት አሸንፏል፡፡

ጠንካራ ፉክክር በታየበት የወንዶች ውድድር አትሌት ሙሉጌታ ከኬንያውያን አትሌቶች ጋር ብርቱ ፉክክር በማድረግ በአስራ አምስት





አትሌት ሙሉጌታ ኡማ እና መስታወት ፍቅር የ2024 የፓሪስ ማራቶን አሸናፊዎች ሆነዋል፣

ሰከንዶች ልዩነት ነው ለድል የበቃው፡፡ የገባበት ሰዓትም በርቀቱ የራሱ ምርጥ ሆኖ ተመዝግቧል፡ ኢትዮጵያዊውን አትሌት ተከትሎ ኬንያውያኑ ቲተስ ኪፕሩቶ በ2:05:48 ሰዓት ሁለተኛና ኤሊሻ ሮቲች በ2:06:54 ሰዓት ሦስተኛ በመሆን አጠናቀዋል፡፡ ሦስተኛ ሆኖ ያጠናቀቀው ሮቲች 2021 ላይ የውድድሩን ክብረወሰን የጨበጠ አትሌት እንደመሆኑ የዘንድሮውን ውድድር የማሸነፍ ትልቅ ግምት ተሰጥቶት ነበር፡፡

በሴቶች መካከል በተካሄደው ፉክክር በርቀቱ ከዚህ ቀደም ስማ የማይታወቀው አትሌት መስታወት ፍቅር ለመጀመሪያ ጊዜ ያደረገችውን ውድድር በ2:20:45 ሰዓት በድል ተወጥታለች፡፡ ሌላኛዋ ኢትዮጵያዊት አትሌት እናትነሽ አላምረው ደግሞ በ2:20:47 ሰዓት የሁለተኛነቱን ደረጃ በመያዝ ውድድሩን ፈፅማለች፡፡ ኬንያዊቷ የረጅም ርቀት የዓለምና የኦሊምፒክ ቻምፒዮን አትሌት ቪቪያን ቼርዮት ወደ ማራቶን ፊቷን ካዞረች ወዲህ የተለያዩ ድሎችን ብታስመዘግብም በዘንድሮው የፓሪስ ማራቶን በሦስት ሰከንድ ልዩነት ተከታትለው ለገቡትን አዳዲስ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች እጅ ሰጥታለች፡፡ ቼሪዮት ውድድሩን በሦስተኝነት ስትፈፅም 2:21:47 ሰዓት አስመዝግባለች፡፡

የ2016 ሪዮ ኦሊምፒክ የ5ሺ ሜትር የወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊና የአራት ጊዜ የዓለም ቻምፒዮና ቼሪዮት ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ የማራቶን ውድድር እንደ ማድረጓና 40 ዓመት ላይ እንደመገኘቷ ያስመዘገበችው ውጤት የሚያስከፋ አይደለም፡፡

በሳምንቱ መጨረሻ ተጠባቂ የሆነው ሌላኛው ትልቅ የማራቶን ውድድር በደቡብ ኮሪያ ዴጉ የተካሄደው ሲሆን ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ሩቲ አጋ የውድድሩን ክብረወሰን በማሻሻል አሸንፋለች። በወንዶች ግን ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ደረጃ ውስጥ መግባት ሳይችሉ ቀርተዋል፡፡

በዓለም አትሌቲክስ የወርቅ ደረጃ በተሰጠው የዴጉ ማራቶን አትሌት ሩቲ አጋ የውድድሩን የቀድሞ ክብረወሰን በ48 ሰከንድ በማሻሻል በ2፡21፡08 ሰዓት ማጠናቀቅ ችላለች፡፡ እሷን ተከትለውም ኬንያውያኑ አንጌላ ቱናይ በ2፡21፡32 እንዲሁም ኤቫሊን ቺርቺር በ2፡22፡12 ሰዓት ሁለተኛና ሦስተኛ ደረጃን በመያዝ ውድድሩን ፈፅመዋል፡፡ የውድድሩ የቀድሞ ክብረወሰን 2፡21፡56 ሲሆን 2022 ላይ በኤርትራዊቷ አትሌት ናዝሬት ወልዱ ተይዞ እንደቆየ ይታወሳል፡፡

በተመሳሳይ እለት በበርሊን በተካሄደው የግማሽ ማራቶን ውድድር ኢትዮጵያውያን አትሌቶች የሴቶቹን ፉክክር አንደኛና ሁለተኛ ሆነው ማጠናቀቅ ችለዋል። አትሌት ሙላት ተክሌ የሃያ አንድ ኪሎ ሜትር ፉክክሩን በ66፡53 በማጠናቀቅ ቀዳሚ ስትሆን ሌላኛዋ ኢትዮጵያዊት ዘራይ ፍታው በ67፡22 በማጠናቀቅ ሁለተኛ ሆናለች፡፡ በዚሁ ውድድር በወንዶች መካከል የተካሄደውን ፉክክር ኢትዮጵያውያን አትሌቶች አቋርጠው ወጥተዋል፡፡


ከኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ጋር በመተባበር በየወሩ የሚታተም

## የኮርፖሬሽኑን ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነት ለማሳደግ

የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ከፍተኛ ፉክክር በበሚስተዋልበት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ውስጥ ግንባር ቀደም ሚና ለመጫወት የተለያዩ ለውጥ አምጭና ተወዳዳሪነትን የሚያሳድጉ ስትራቴጂዎችን ቀይሷል፡፡ ይህንን ተግባራዊ በማድረግም በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ የገበያ አድማሱን እያሰፋና ትርፋማነቱን ለማስቀጠል እየሰራ ይገኛል።

በተለይም ኮርፖሬሽኑ ተሰማርቶባቸው በሚገኝባቸው በዋና ዋና የመሠረተ ልማት ግንባታዎች ማለትም በመንገድ፣ በድልድይ፣ በአውሮፕላን ማረፊያ፣ በሕንፃ ግንባታ፣ በግድብ፣ በመስኖና ውሃ አቅርቦት፣ በኮንስትራክሽን ግብዓቶች ማምረት እንዲሁም በፕሮጀክት ዲቨሎፕመንትና ማኔጅመንት፣ በዲዛይንና ኢንጂነሪንግ አገልግሎት እና በኮንስትራክሽን ማሽነሪዎችና መሳሪያዎች መገጣጠምና ጥገና ሥራዎች ላይ ውጤታማ ለመሆን ተግቷል፡፡

በዚህም ከ2012 በጀት ዓመት ጀምሮ እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉና የኮርፖሬሽኑን ሁለንተናዊ አቅም የሚያሻሽሉ የተለያዩ የሪፎርም ሥራዎችን በተለያዩ ምዕራፎች ተግባራዊ በማድረግ ከፍተኛ ውጤት አስመዝግቧል፡፡

በመጀመሪያው የሪፎርም ምዕራፍ በተለያዩ የሥራ ክፍሎች መካከል ያለውን አንድነት ለማረጋገጥና የተቀመጡ ግቦችን እውን ለማድረግ ተቋማዊ ሪፎርም አከናውኗል። በሁለተኛው ምዕራፍ ተግባራዊ የተደረገው የፕሮጀክት ማኔጅመንት ሪፎርም ሲሆን ይህም የፕሮጀክቶችን አፈፃፀምና ትርፋማነታቸውን ለማሻሻል አስችሎታል። ኮርፖሬሽኑ ተግባራዊ ያደረገው ሦስተኛውን ሪፎርም ኢንዱስትሪላይዜሽን እና ዲጂታላይዜሽን ሲሆን የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ስርዓትን ለማሻሻል ትልቅ ሚና ነበረው፡፡

አራተኛውና የዚህ ፅሁፍ ማዕከል ደግሞ ኢንተርናሽናላይዜሽን ሪፎርም ሲሆን ኮርፖሬሽኑ በዓለም አቀፍ የኮንስትራክሽን እና የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ እና ተመራጭ ኩባንያ እንዲሆን ለማስቻልና የገበያ አድማሱን ለማስፋት የኮርፖሬሽኑን ራዕይ አንኳር ጉዳዮች በጥናት በመለየት ወደስራ የተገባ ሲሆን በዚህም ለኮርፖሬሽኑ ትልቅ አቅም ተፈጥሮለታል፡፡

የግንባታ ጥራት እና አፈጻጸምን ለማሳደግ ቁልፉ ጉዳይ ብቃት ያላቸው የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶችን የሚመሩ የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጆች በኮርፖሬሽን እና በሀገር ደረጃ ማፍራት ሲቻል ነው፡፡ በመሆኑም ኮርፖሬሽናችን የኮንስትራክሽን ሙያተኞች ማበልጸጊያ ኢንስቲትዩትን በማቋቋም በዘርፉ ከፍተኛ የሥራ ልምድና የጠለቀ ዕውቀት ያላቸው የሀገር ውስጥ የውጭ ምሁራንን ጭምር በመጋበዝ በኢንስቲትዩቱ ስልጠና መስጠት ጀምሯል። ተመሳሳይ ስልጠናዎችን ከሚሰጡ የውጭ ተቋማት ጋር በፈጠረው ግንኙነት እና የመግባቢያ ስምምነት መሰረት ዕውቀትና ክህሎትን የሚያሳድጉ ስልጠናዎች በዙም መስጠት ተችሏል፡፡

ኮርፖሬሽኑ የገበያ ተወዳዳሪነትን እና ተመራጭነትን ለማሳደግ በተመረጡ የሀገራችን ክፍሎች በአሁኑ ወቅት አራት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን በከምቦልቻ፣ በአርባምንጭ፣ በጅማ እና በድሬዳዋ ከተሞች አቋቁሟል። በምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ የገበያ አድማሱን ለማስፋትም በጂቡቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ተከፍቶ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡ በኬንያ፣ በሩዋንዳ፣ በደቡብ ሱዳን፣ በደቡብ አፍሪካ እና በሶማሌ ላንድ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ለመክፈት በሒደት ላይ ይገኛል፡፡

ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነትን ማሳደግ በራሱ ለሀገር የውጭ ምንዛሬን ለማስገኘት ከሚኖረው ጥቅም ባሻገር ከሌሎች ሀገራት እና ኩባንያዎች ጋር በመስራት የሚገኘውን ተቋማዊ ልምድ እና የሙያተኞች ክህሎትን ያሳድጋል። በተጨማሪም በሀገር ውስጥና በውጭ በተከናወኑ ዓለም አቀፍ አውደ ርዕዮች እና ቢዝነስ ፎረሞች በመሳተፍ ሰፊ ልምድ መቅሰም አስችሎታል፡፡

ኮርፖሬሽኑ የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን በራሱ አቅም በማምረት ለራሱ ፍጆታ ከመጠቀም ባለፈ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ለማቅረብ እያደረገ ባለው ጥረትም የውጭ ምንዛሬ ወጪን ለመቀነስ አስችሎታል፡፡ ፕሮጀክቶችን በጥራት እና በተያዘላቸው ጊዜ ለመጨረስ ጠቅሞታል። ስለሆነም ኮርፖሬሽኑ የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ማምረቻ ዘርፉን አቅም በከፍተኛ ደረጃ በማጠናከር በውጭ እና በሀገር ውስጥ በኮንስትራክሽን ግብዓቶች ማኑፋክቸሪንግ መስክ ተወዳዳሪ ኩባንያ ለመሆን ጭምር ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል፡፡

ከኢንተርናሽናላይዜሽን ሪፎርሙ ባሻገር የኢንቨስትመንት ሪፎርም ተግባራዊ በማድረግ ላይ ነው፡፡ በዚህም አዳዲስ መስኮች ላይ ለመሰማራት እየሰራ ይገኛል፡፡ በተለይም በቤቶች እና ሪል እስቴት ልማት በመሰማራት የገበያ አድማሱን ከማስፋት በተጨማሪ በሀገር ዕድገትና ብልጽግና የኮርፖሬሽኑን አሻራ ለማሳረፍ እየሰራ ይገኛል፡፡

በአጠቃላይ ከ2012 በጀት ዓመት ጀምሮ ኮርፖሬሽኑ ተግባራዊ ባደረጋቸው የሪፎርም ስራዎች በመታገዝ የተሻለ የገቢ እና የትርፍ ዕቅድ አፈጻጸም አስመዝግቧል። ይህም ኮርፖሬሽኑ ዓለምአቀፋዊ ተወዳዳሪነቱን ለማረጋገጥ በሚሠራቸው ሥራዎች ላይ ትልቅ አቅም ፈጥሮለታል፡፡